**DSpace Institution**

**DSpace Repository** **http://dspace.org**

Ethiopian Languages and Literature - Amharic Thesis and Dissertations

2021-09-21

# þÿ `( 5 sÊ è - e u ¨ •ef (óu } þÿ - ë Í pÛ öd `Ø •› -M p *Î} p p

þÿ ` 0 Ê u ` `

http://ir.bdu.edu.et/handle/123456789/12625

*Downloaded from DSpace Repository, DSpace Institution's institutional repository*

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂውማኒቲስ ፋኩሊቲ

የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ፤ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በሰላማዊት አበበ

መስከረም፣ 2014 ዓ.ም

ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ

# ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ

ሂውማኒቲስ ፋኩሊቲ

ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

አማርኛ ቋንቋ ማስተማር (TeAm) ለተባለው መረሃ ግብር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ የምርምር ጥናት

በሰላማዊት አበበ

አማካሪ፤

ዘውዱ መብሬ (ዶ/ር)

መስከረም፣ 2014 ዓ.ም

ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ

**ባህርዳር ዩኒቨርስቲ**

**ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል፣**

**ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

'ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃት ከአንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ፤ በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በኢሉ-ገላን ወረዳ በኢጃጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል፤ አማርኛ ቋንቋ ማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ በሰላማዊት አበበ የቀረበው ይህ ጥናት በውጭና በውስጥ ፈታኞች ተገምግሞ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

**የፈታኞች ማረጋገጫ**

የአማካሪ ስም፤ ዶ/ር ዘውዱ መብሬ ፊርማ፤ ________ ቀን፤ 11/01/2014 ዓ.ም

የውጭ ፈታኝ ስም፤ ዶ/ር በለጠ ያዕቆብ ፊርማ፤ _________ ቀን፤ 11/01/2014 ዓ.ም

የውስጥ ፈታኝ ስም፤ ዶ/ር መለሰ ገላነህ ፊርማ፤ ________ ቀን፤ 11/01/2014 ዓ.ም

# ማረጋገጫ

ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ያዘጋጀሁት እኔ ሰላማዊት አበበ መሆኔን እያረጋገጥኩ በጥናቱ የተጠቀምኩባቸው ድርሳናት ዋቢነታቸው በትክክል የተጠቀሰ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአጥኝዋ ስም፤ ሰላማዊት አበበ ሐደሮ

ፊርማ፤_____________

ቀን፤ 10/01/2014 ዓ.ም

ተማሪ ሰላማዊት አበበ በኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል አማርኛን በማስተማር (TeAm) የድህረ ምረቃ ተማሪ ስትሆን የጥናት ስራዋን ከአማካሪዋ ጋር በመተባበር ስትሰራ ቆይታለች፡፡ ስለሆነም ጥናታዊ ጽሁፉ የተጠናቀቀ በመሆኑ ለፈተና እንዲቀርብ ተስማምቻለሁ፡፡

የአማካሪ ስም፤ ዶ/ር ዘውዱ መብሬ

ፊርማ፤ ______________

ቀን፤ 10/01/2014 ዓ.ም

# ምስጋና

ይህን ቀን እንዳይ ለረዳኛና ጤናዬን ለሰጠኝ ለቅድስት ድንግል ማሪያም ልጅ ለጌታችን ለመድሃኒታችን ለእየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁንልኝ። ይህን ጥናት ተጀምሮ እስከጠናቀቅ ድረስ ውድ ጊዜያቸውን ስውተው ፅሁፉን በጥልቀትና በጥንቃቄ በማረም ሀሳቦችን በመስጠት የቅርብ ክትትል ላደረጉልኝ መምህሬና አማካሪዬ ለዶ/ር ዘውዱ መብሬ የማቀርበው ምስጋና ከፍ ያለ ነው። በመቀጠልም በትልመ ጥናቱና በዋናው ጥናት ጊዜ ጠቃሚ ምክርና ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠት ከመሰረቱ እንዲስተካከል አስተዋጽኦ ላበረከቱት መምህሬ ዶክተር ማስተዋል ውበቱ ያለኝ ምስጋና ላቅ ያለ ነው።

ጥናቱን በማካሂድበት ጊዜ መረጃዎችን በመስጠትና በመገምገም ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ደጋግመው በማንበብና በማስተካከል ሙያዊ እገዛና በሚያስፍልገኝ ሁሉ ከጎኔ ለነበሩ ጓደኞቼ ለበሪሁን አድማሱ፣ ለዮሐንስ አማረ፣ ለዳምጠው ሙጨ፣ ለጠይባ ወዳጅ፣ ለራሙቴ ናስር፣ ለለይላ ሙዘሚል፣ ለፍሬ ነጋሽ እና ለእህቴ መስከረም አበበ ምስጋናዬን አቀርባለው።

እንዲሁም በጽሁፍ እና ልጆቼን ሰብስቦ የእናትነት ፍቅር በሚያስፍልጋቸው ጊዜ ሁሉንም ቦታ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል በመሸፍን ለረዳኝ ለውድ ባለቤቴ መምህር ባይሳ ዱጋሳ ምስጋና ባቀርብ ማራቅ ስለሚሆንብኝ በማስተርስ የትምህርት ህይወቴ ትልቅ ቦታ ስላለው ማመስገን ይቅርብኝ፤ ከዛም በፀሎቷ ላገዘችኝ ውድ እናቴ ወ/ሮ እህትአገኘው ወ/ ዮሐንስ አመስግናለው ኑርልኝ። በመጨረሻም በሞራል እና በልዩ ልዩ ስራዎች እገዛና ትብብር ላደረጉልኝ የኢጃጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አመራሮችና በዚህ ጥናት ለመሳተፍ ፍቃደኛ ለሆኑት ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች እና የቁሳቁስ ድጋፍ ለተባበረኝ መምህር በሪሁን አድማሱ የላቀ ምስጋና አቀርባለሁ።

# አህጽሮተ ጥናት

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በተማሪዎች ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃቶችና የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው። በመሆኑም ተዛምዷዊ የምርምር ስልትን ተከትሏል። የጥናቱ ተሳታፊዎች በምዕራብ ሸዋ ዞን በኢሉ-ገላን ወረዳ በኢጃጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል በ2013 ዓ.ም ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል በተራ እጣ ናሙና የተመረጡ 100 ተማሪዎች ናቸው። የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስም በጽሁፍ መጠይቅና በአንብቦ መረዳት ፈተና ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል። በጥናቱ ተሳታፊዎች ራስን የማበረታታት፣ ጭንቀትን የመቀነስ፣ በትብብር የመስራትና የመጠየቅ ብልሃት አጠቃቀም መካከል ጉልህ ልዩነት ታይቷል። በተጨማሪም በማህበረስሜታዊ የመማር ብልሃትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል አዎንታዊ የሆነ ጉልህ ተዛምዶ ታይቷል። በመጨረሻም ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃትን የአንብቦ የመረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻቸው ጉልህ መሆኑን አሳይቷል። ስለዚህ መምህራን አንብቦ መረዳት ችሎታን በሚያስተምሩበት ጊዜ በማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩን በመረዳት የተማሪዎችን ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃቶችን አጠቃቀም ግምት ውስጥ ቢያስገቡ የተሻለ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል።*

# ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምስጋና ..... i
አህጽሮተ ጥናት ..... ii
ማውጫ ..... iii
ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ ..... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ..... 1
1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር ..... 5
1.3 የጥናቱ ዓላማዎች ..... 8
1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት ..... 8
1.5 የጥናቱ ወሰን ..... 8
1.6 የጥናቱ ውሱንነት ..... 9
1.7 የቁልፍ ቃላት ብያኔ ..... 9
ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት ..... 10
2.1. ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ምንነት ..... 10
2.1.1 የቋንቋ መማር ብልሃቶች ንድፈ ሃሳብ ..... 10
2.1.2 የቋንቋ መማር ብልሃቶች ባህሪያት ..... 13
2.1.3 የማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ምንነት ..... 13
2.1.4. የማህበረ ስሜታዊ ክፍሎች ..... 15
2.1.4.1 የመጠየቅ ብልሃት ..... 15
2.1.4.2 ራስን የማበረታታት ብልሃት ..... 16
2.1.4.3 በትብብር የመስራት ብልሃት ..... 16
2.1.4.4 ጭንቀት የመቀነስ ብልሃት ..... 18
2.2. የማህበረ ስሜታዊ ብልሃትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ንድፈ ሃሳባዊ መሰረት ..... 18
2.3. አንብቦ የመረዳት ምንነት ..... 19
2.3.1. አንብቦ የመረዳት ብልሃቶች ..... 22
2.4. አንብቦ ለመረዳት የጥሩ አንባቢ ባህርያት ..... 23
2.5. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃዎች ..... 25

ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ንድፍና ዘዴ ........ 26
3.1 የጥናቱ ንድፍ ........ 26
3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ ........ 26
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 27
3.3.1 የጽሁፍ መጠይቅ ........ 27
3.3.2 አንብቦ የመረዳት ፈተና ........ 28
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 29
ምዕራፍ አራት፤ የውጤቱ ትንተና እና ማብራሪያ ........ 31
4.1 የመረጃ ትንተና ........ 31
4.2 የውጤት ማብራሪያ ........ 34
ምዕራፍ አምስት፡ ማጠቃለያ፤ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳብ ........ 36
5.1 ማጠቃለያ ........ 36
5.2 መደምደሚያ ........ 37
5.3 የመፍትሄ ሀሳብ ........ 37
ዋቢዎች ........ 38
አባሪዎች ........ 43
አባሪ ሀ፤ የማህበረ ስሜታዊነት የመማር ብልሃት የፅሁፍ መጠይቅ በአማርኛ እና በዝንግሊዝኛ ቋንቋዎች ........ 43
አባሪ ሀ1፤ የማህበረ ስሜታዊነት የመማር ብልሃት የፅሁፍ መጠይቅ በአማርኛ ቋንቋ ........ 43
አባሪ ሀ2፤ የማህበረ ስሜታዊነት የመማር ብልሃት የፅሁፍ መጠይቅ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ........ 46
አባሪ ለ. የአንብቦ መረዳት ፈተና ........ 48
አባሪ ሐ፤ የጽሁፍ መጠይቁና የአንብቦ መረዳት ፈተናው አስተማማኝነት ፍተሻ ........ 54
አባሪ ሐ1፤ የጽሁፍ መጠይቁን አስተማማኝነት በክሮምባህ አልፋ ለመለካት ሲባል በሙከራ ጥናቱ ወቅት የተሰበሰበ መረጃ ........ 54
አባሪ ሐ2፤ አንብቦ መረዳት ፈተናውን አስተማማኝነት በKuder-Richardson (KR-20) ለመለካት ሲባል በሙከራ ጥናቱ ወቅት የተሰበሰበ መረጃ ........ 55
አባሪ መ፤ በጽሁፍ መጠይቅ እና በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰቡት የዋናው ጥናት መረጃዎች እሙኖች ፍተሻ መረጃዎች ........ 56
አባሪ መ1፤ በጽሁፍ መጠይቅ እና በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰቡት የዋናው ጥናት መረጃዎች የስርጭት ወጥነት ፍተሻ ........ 56

አባሪ ሐ2፧ ተንባይ ተላውጦዎች ከተተንባይ ተላውጦ ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ ያላቸው ስለመሆኑ ............ 56
የተካሄደ የብትን ግራፍ ፍተሻ፧ ............ 56
አባሪ መ3፧ የፈርጀብዙ ተዛምዶ (multicollinearity) አለመኖር ፍተሻን ውጤት ............ 57
አባሪ መ4፧ Homoscedasticity (በነጻ ተላውጦዎቹ ባለው እያንዳንዱ ዋጋ ትይዩ በጥገኛው ተላውጦ የሚገኙ ዋጋዎች መደበኛ ልይይት ተመሳሳይነት) ፍተሻ ውጤቶች .. 57
አባሪ ሠ፧ በጽሁፍ መጠይቅ እና በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰቡ የዋናው ጥናት መረጃዎች ............ 60
አባሪ ሠ1፧ በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ የዋናው ጥናት መረጃዎች ............ 60
አባሪ ሠ2፧ በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰቡ የዋናው ጥናት መረጃዎች ............ 62

# ምዕራፍ አንድ፤ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ መማር ብልሃት ምንነትን ለመግለጽ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ እንደሌለ ፀሀፍት ያስረዳሉ አሊስ (1994)። በመሆኑም በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች (ሩቢን ፣ 1987 ፤ኦክስፎርድ ፣ 1990 ፤ ኦማሌና ቻሞት ፣ 1990) የራሳቸውን ብያኔ እንደሰጡ የአሊስ (1994) ገለፃ ያስረዳል።

እንደ ሩቢን (1987) ገለፃ የቋንቋ መማር ብልሃቶች ተማሪዎች የሚመሰሩትን የቋንቋ ስርአት ለማሳደግ የሚረዱና በቋንቋ መማር ላይ በቀጥታ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ብልሃቶች ናቸው። የኦማሊና ቻሞት (1990) ብያኔ የሚያሳየው ደግሞ የቋንቋ መማር ብልሃቶች የቋንቋ ተግባቦታዊ ችሎታን ንቁና በራስ የሚመራ ተሳትፎ ለማሳደግ የሚረዱ መሳሪያዎች መሆናቸውን ነው።

እንደ ኦክስፎርድ (1990) ገለፃ ደግሞ ቋንቋ የመማር ብልሃቶች ተማሪው የትምህርቱን ሂደት ቀላል፣ ፈጣን፣ ይበልጥ ማራኪና ምቹ፣ ራስ መርና ግልፅ ለማድረግ ፣ ወደ ተሻለና አዲስ ክንውን ለመሻገር የሚወስዳቸው የተወሰኑ እርምጃዎች ናቸው።

ቋንቋን የመማር ብልሃቶች በተማሪዎች የሚተገበሩ፣ እውቀት ማካበትን ፣ ሀሳብ አስታውሶ መጠቀምን የሚያፋጥኑ የአሰራር ባህሪዎች፣ ተግባራዊ ደረጃዎች ናቸው። እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው የቋንቋ ትምህርቱን ሂደት ምቹ ፣ ራስመርና አስደሳች በሆነ መንገድ ለመወጣት የሚያስችሉት መንገድ ነው።ይሁን እንጂ ቋንቋን እንዴት ባለ ብልሃት መማር እንደሚያስችል ጥናቶች እንደሚያስፈልጉ አመለካተዋል። (ሳክ እና ሌሎች፣1997) ።

በቋንቋ መማር ብልሃቶች አጠቃቀም ዙሪያ ጥናት ማድርግ የተጀመረው በ1960ዎቹ ገደማ እንደሆነ ዊልያም እና በርደን 1997 ይገልፃሉ። በ1970ዎቹ የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶት እንደነበር በአልአክባሪና ሀያት ዘዲያ (2008) የተጠቀሱት በሩቢን (1987) ሰርተን (1983) ስራዎች ያመለክታሉ። ቻሞት (1990) እና ኦክስፎርድ (1990) ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ በቋንቋ የትምህርት መስክ መምህራን በማስተማር ላይ ከማተኮር ይልቅ በተማሪዎችና በመማር ላይ እያተኮረ መምጣቱን እንደሚገልፁ የሲንግ (2004) ገለፃ ያስረዳል። በዚህ መሰረት አንብቦ መረዳት የሚችሉ ተማሪዎች ክህሎታቸውና ብቃታቸውን ለማሻሻል በርካታ የቋንቋ መማር

ብልሃቶች ይጠቀማሉ። እንደነዚ አይነት ጥናቶች ደግሞ የቋንቋ ተማሪዎች ከጥገኝነት ነፃ የሆነና በራስ የሚመራ ብልሃትን ለመጠቀም ለራሳቸው መማር ሀላፊነት እንዲወስዱ ወደ ማድረግ እየተሸጋገሩ መምጣታቸውን የኦክስፎርድ (1990) ጥናት የሚያሳይ መሆኑን አልአክባሪና ሀያት ዘዲያ (2008) ይገልፃሉ ።

ቋንቋን በመማር ረገድ በተለይ ሁለተኛ ቋንቋን እንዴት መማር አለብን? እንዴትስ ቋንቋውን ማሳደግ እንችላለን? የሚሉ አብይ ጥያቄዎች በተማሪዎች ተደጋግመው ይነሳሉ። ይሁንእንጂ ለእነዘህ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ማገኘት አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ጥያቄዎችን መነሻ በማድርግ ብራውን (2006) ቋንቋን እንዴት መማርና ማሳደግ እንደሚቻል የሚጠቅሙ በርካታ ብልሃቶች መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡ ይሁንእንጂ የቋንቋ መማር ብልሃቶችን በተመለከተ በብዛት ምርምር ማድረግ የተጀመረው በ1960ዎቹ ገደማ ነው፡፡ ይህም ከአእምሯዊ የስነባህሪ እድገት ጋራ ተያይዞ የመጣ ነው፡፡ ዊሊያምስና በርደን (1997) ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በየዘመኑ የተለያዩ መስፍርቶች ላይ በመመስረት የቋንቋ መማር ብልሃቶችን ለመከፋፍል ተሞክሯል፡፡ በኢሊስ (1994)፣ ብራውን (1994) እና ኦክስፎርድ (1990) የቋንቋ መማር ብልሃቶችን ከፋፍለው ለማሰየት ሞክረዋል፡፡ ክፍፍሎቹ ግን ከሞላ ጎደል በመሰረታዊ ሀሳብ ደረጃ ተመሣሣይ ማእቀፍ ያላቸው መሆኑን ኢሊስ (1994)፣ ብራውን (1994) እና ዊሊያም እና በርደን (1997) ይገልፃሉ፡፡

ኢሊስ (1994) በሩቢን (1987) አከፋፈል መሰረት ተማሪዎች በቋንቋ መማር ወቅት የሚጠቀሟቸው ሦስት አይነት ብልሃቶች እንዳሉ ተመላክቷል፡፡ እነዚህም ብልሃቶች የመማር ብልሃቶች ተግባቦታዊ ብልሃቶች፣ ማህበራዊ ብልሃቶች፣ ስሜታዊ ብልሃቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ብራውን (1994) እና ኢሊስ (1994) እንደሚገልጹት የቋንቋ መማር ብልሃቶች ልዕለ እምሯዊ፣ አእምሯዊና ማህበረ ስሜታዊ በመባል በሦስት ምድቦች ይክፍሏቸዋል፡፡

በዊሊያምስ በርደን (1997) እና በበራውን (1994) በተጠቀሰው በኦክስፎርድ (1990) አክፍፍል ደግሞ ቀጥተኛ እና ኢቀጥተኛ ያልሆኑ ስድስት የቋንቋ መማር ብልሃቶች እንዳሉ ተመላክቷል፡፡

ከላይ በቀረቡት አከፋፈሎች መካክል የኦክስፎርድ (1990) አክፋፋል ከሌሎች አከፋፋል የተሻለ ዝርዝር እንደሆነ በአልአክባሪና ሀያት ዘዲያ (2008) ጠቀሰው ያስረዳል፡፡ የዊሊያምስ በርዳን (1997) ሀሳብ የሚያሳየውም ይህንን የኦክስፎርድ (1990) አከፋፋል ከዚህ በፊት በነበሩት አከፋፋል የተካተቱ አብዘኞቹ ባህሪያት አጠቃሎ የያዘና የበለጠ ዝርዝር አክፋፋል መሆኑ ነው፡፡

ይህም በመሆኑ በአሁኑ ሰአት የኦክስፎርድ (1990) ሞደልና የብልሃት መጠይቅ ለቋንቋ መማር ብልሃቶች ምርምር መሰረት ሆኖ በማገልገል ላይ ያለ መሆኑን አልአክባሪ እና ሀያት ዘዲያ (2008) ይገልፃሉ። ኦክስፎርድ (1994)፤ ኢሊስ (1994) እና ዊሊያምስና በርደን (1997) የቋንቋ መማር ብልሃትን በሁለት ዋና ዋና ብልሃቶች ቀጥተኛ ብልሃትና ኢቀጥተኛ ብልሃት ተብለው እንደሚከፈሉ የኦክስፎርድ (1990) አከፋፋልን ዋቢ በማድረግ ይገልፃሉ። ቀጥተኛ ብልሃት የሚባሉት የማስተዋል፣ አእምሯዊ፣ የማካካስ ብልሃት ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች የሚማሩትን የቋንቋ ብልሃት በማሳደግ ረገድ ክፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ብልሃቶች እንደሆኑ የዊሊያምስ እና በርደን (1997) እንደሁም ብራውን (1994) ገለፃ ያመለክታል። ከዚህም በተጨማሪም እነዚህ ብልሃቶች በቋንቋ መማር ወቅት በቀጥታ የሚተገበሩ እና ታላሚውን ቋንቋ መጠቀምን የሚያመላክቱ ናቸው። ኢቀጥተኛ ብልሃት የሚባሉት ደግሞ የመገንዘብ ወይም የመረዳት፣ ስሜታዊ፣ ማህበረዊ ብልሃቶች ናቸው። እነዚህ ብልሃቶች መማርን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያግዙ ብልሃቶች ናቸው በማለት ዊሊያምስ እና በርደን (1997)፣ ብራውን (1994) ይገልፃሉ።

ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ይበልጥ እየታወቀ የመጣው በ1980ዎቹ ነው። የዚህ እውቀት የመጀመሪያ አመንጭዎች መካከል ኦ.ማሌይ፣1990፤ ቻሞት1990 እና ኦክስፎርድ፣1991 ናቸው። (ጃያንቴ ቪጃያ፣ 2012) ።

እንደ ኦክስፎርድ (1990) ገለጻ ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት የምንላቸው በተፈጥሮ ከመደበኛው ትምህርት ውጭ የሆኑ፣ በተማሪውና በመምህሩ መካከል ያለውን መተሳሰብ፣ የሰው ችግር እንደራስ ችግር በማየት ስር የሰደደ ግንዛቤ እንዲኖረን የሚያደርጉ ብልሃቶች ናቸው። ስሜታዊነትና አመለካከት ያላቸውን ተፅዕኖ ከግምት በማስገባት የሚቀርቡ ብልሃቶች ናቸው። ኦክሰስፎርድ (1990) ማህበረ ስሜታዊ ብልሃቶች ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ እንዴት ያለ ስሜት እንደሚሰማቸው እያሰቡና ከሌሎች ጋር እየተረዳዱ ሲማሩ ማህበረ ሰሜታዊ ብልሃቶችን ተጠቀሙ እንላለን። ይህን ስልት እርስ በርስ በመረዳደት እና ያልተረዱትን ከሌላ ወገን /ከጓደኛ/ ከመምህር፣ ከማህበረሰብ በመጠየቅ የሚካሄድ የመማር ብልሃት ነው። በመተጋገዝና አብሮ በመሰራት የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታማ እንዲሆነ ይናገራል። ተማሪው ወይም መምህሩ ሊቀርፏቸው የሚገባቸው ስሜት ነክ ጉዳዩች የሚከተሉት ናቸው። ምሳሌ፡ ጭንቀት፤ የናረ ጉጉትን፣ ፍርሃት፣ ቁጡነት፣ አለመረጋጋት፣ በሀሳብ አለመተማመንና ሌሎችም እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ለሁለተኛ ቋንቋ መማር ሂደት ከፍተኛ ዋጋ አላቸው። እንደ ብራውን (2002)

ገለፃ ይህ ስልት ተማሪዎች ሁሉ ለእርስ በርስ ተራክቦ የሚያጋልጥ በመሆኑ በአከባቢያቸው ባለው ነገር ሁሉ መሳተፍቸው የቤተሰባዊነት፣ የጓደኛነት መንፍስ ስለሚሰማቸው ጎጂ ማህበረዊና ስሜታዊ ጉዳዩች ቦታ ያጣሉ። እንደ ኦማይሊ እና ቻሞት (1990)። አፍርሽ ስሜት ነክ ተለውጦዎችን መቆጣጠር የሚቻለው ከአቻ ጓደኛ ጋር በመረዳደት ከሌሎች ጋር አዎንታዊ መስተጋብር በመፍጠር፣ የእርስ በርስ ተሳትፎና ያልተረዱትን በማብራራትና በመጠየቅ፣ ከራስ ጋር በመነጋገርና ራስን ማበረታታት ነው። ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ መማር የተሻለ ውጤት የሚያሳዩት በክፍል ውስጥ ሁኔታ በመተጋገዝ እና አብሮ በመስራት ላይ በተመሰረተ የመማር ሂደት ያለፉ ናቸው። ይህ የሚያሳየው የቤተሰብ፣ የአካባቢ፣ የክፍል ውስጥ ሁኔታ በተማሪዎች ውጤት ላይ በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ ማሳደር እንደሚችል ነው።

እንዲሁም ስለ መማር ብልሃት ምንነት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ያደረጉት ኦክስፎርድ (1990) ሲሆኑ እሳቸውም የመማር ብልሃት በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ብለው ከመደቡ በኋላ በቀጥተኛ ብልሃት ስር ታላሚውን ቋንቋ የማስታወስ ብልሃት፣ ግንዛቤያዊ ብልሃትና የማስተካኪያ ብልሃት የሚሉ ዝርዝር ነጥቦች እንዳሉ ይገልፃሉ። ብልሃቶቹም የተማሪዎችን የመማር ዝንባሌ እንደሚጨምሩ ተመራማሪው አክለው ያስረዳሉ። በኢቀጥተኛ የመማር ብልሃት ስር ደግሞ ልዕለአእምሮኣዊ ግንዛቤ፣ ማህበራዊና ስሜታዊ ብልሃቶች ሲገኙ ማህበራዊና ስሜታዊ ብልሃቶች ተጣምረው ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት እንደሚባሉ አስረድተዋል፣ በስሜታዊ ብልሃት ተማሪዎች ለመማር አስበው፣ አቅደው፣ ራሳቸውን ተቆጣጥረው፣ ገምግመውና አስተካክለው በትምህርታቸው ስኬታማ እንዲሚሆኑ ኦክስፎርድ (1990) ያስረዳሉ። በመቀጠልም በልዕለ አእምሯዊ ብልሃት ደግሞ ተማሪዎች በግል ወይም በቡድን ሆነው ከመረዳት እስከ ማብራራት ብሎም እስከ መተንበይ እንደሚደርሱ ይገልፃሉ። እንዲሁም በማህበራዊ ብልሃት ተማሪዎች ከማህቢረሰቡ ጋር ጥብቅ መስተጋብር ፈጥረው ሊማሩ እንደሚችሉ ኦክስፎርድ (1990) ይገልፃሉ። ይሁንእንጂ ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት በቋንቋ ንባብ ረገድ ማህብራዊ ጠባይ ሲኖር ማህበራዊ ብልሃት ደግሞ በተማሪዎች ላይ የጭንቀት፣ የፍርሃት፣ የስኬት አልባነት ችግር ሊያስከትል እንደሚችል ኦክስፎርድ (1990) አክለው ያስረዳሉ።

ተማሪዎች ከአሉታዊ አመለካከት፣ ከፍርሃት፣ ከጭንቀት፣ ከብቸኝነትና ከበታችኝነት ስሜት ነፃ ሆነው መማርና ስኬታማ መሆን የሚችሉት በምን አይነት ብልሃት ሲማሩ ነው? በሚለው

ዙሪያ በአሜሪካ በርካታ ጥናቶች ተካሂደዋል። በዚህም መሰርት በኤቫንስ፣ በፓሎምባስ፣ በቤሪማን ከተካሄደው ጥናት የተገኘው የተማሪዎች መልስ የሚከተለውን ይመስላል (ጉኒንግ1996፣110) ።

> በአንደኛ ደረጃም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን እከታተል ነበር። ይሁንእንጂ ብዙ ጊዜ ሰበብ እየፈለግኩ ከትምህርት ቤት እቀር ነበር። ምክንያቴ ደግሞ ጥያቄ በምጠይቅበት ጊዜ ተማሪዎች ይስቁብኛል፤ መምህሩ ደግሞ ዝም ይላል። በዚህ የተነሳም በጭንቀት ውስጥ መሆንና የበታችነት ስሜት ይሰማኝ ስለነበር በውሸት አሞኛል በሚል መፀዳጃ ቤት ሄጄ እደበቅ ነበር። ቀስ በቀስም መምህሩንና ተማሪዎችን ጠላኋቸው።

ከላይ ከቀረበው የተማሪዎች የጥናት ግኝት መረዳት የሚቻለው ማህበራዊ ብልሃት ጭንቀትን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ አስተጽኦ እንዳለው መረዳት ይቻላል። በመሆኑም በዚህ ወቅት መምህሩ ተማሪዎቹን በቅርብ እየተከታተለ ድጋፍ ማድርግ እንደሚገባው ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች ውስጥ ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃት በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ለመረዳት ተችሏል። በመሆኑም ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃት ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን ምርምሮችን ማካሄድ ተገቢ ይሆናል። ይህ ጥናትም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ ይመረምራል።

## 1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር

ማህበረ ስሜታዊ ብልሃትን በተመለከተ በቅርብ የተካሄዱ ጥናቶች (ለምሳሌ:- (ከቾይ፣ 2011፤ ሂስማኖግሉ፣ 2000 እና በአከዬ 2012) እንደሚያመለክቱት ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ በትክክል ለመጠቀም ምን ያህል ጥረት እንደሚያደርጉ አጥኝዎቹ በመማር ብልሃት ዙሪያ ጥናት አድርገዋል። የጥናታቸውም ዋና ሐሳብ ተማሪዎች ከክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ በሚያደርጉት የመማር መስተጋብርን እና ግላዊ ጥረታችውን በዋናነት በመውሰድ በየትኛው ብልሃት ቢጠቀሙ ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ጥናቶች ያመላክታሉ። ለምሳሌ:- በክፍል ውስጥ በሚደረግ የመማር ማስተማር ግንኙነት መምህሩ ተማሪውን መርጦ እንዲናገሩ ሊጠይቃቸው ይችላል ወይም አንዳንድ ተማሪዎች በራሳቸው ጊዜ በድፍረት ደግመው ደጋግመው ጥያቄ ሊመልሱ ይችላሉ። በአንፃሩ ምንም የማይመልሱ ተማሪዎች ደግሞ ሊኖሩ

ይችላሉ፡፡ አንደንዶቹ ደግሞ ጭራሹን አይን አፋር ይሆኑና በፍርሃት ሊዋጡ ይችላሉ፡፡ በዚህን ጊዜ መምህሩ አስፈላጊውን የመማር ብልሃት ተጠቅሞና ጊዜ ወስዶ ተማሪዎቹን ለየብቻ በመጥራት በቃል ምልልስ መልኩ እንዲግባቡ ዕድል ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ ማህበራዊ ተግባቦታቸውን እንዲያሳድጉ ሊመክራቸው ይችላል፡፡ ይሁንእንጂ አንዳንድ ተማሪዎች የመማር ብልሃቱን የመጠቀም ችሎታቸው ቀዝቃዛ ሊሆን ይችላል፡፡ ቢሆንም ዳሩ ግን የተማሪዎች ማህበራዊና ስሜታዊ የመማር ብልሃት እንደገና እየጨመረና እየዳበረ ሲሄድ ከመሰሎቻቸው ጋር ለመግባባት ከፍተኛ ልምምድና ጥረት ያደርጋሉ፤ ጉጉትም ያሳድርባቸዋል፡፡ ቀስ በቀስም የመማር ብልሃት አጠቃቀማቸው እየጐለበተ ሲሄድ በትምህርታቸው ስኬታማ ሊሆኑ ይችላሉ (ዲክ እና ካትብሌን፣ 1991) ፡፡

ዲክና ካት ብሌን፣ (1991) ባካሄዱት ጥናት መሰረት መምህሩ እንደ ትራፊክ መሃል መስመር ላይ ሆኖ ተማሪዎች መሄድ በሚገባቸው ትክክለኛ መስመር ሄደው እንዲማሩ አቅጣጫ በማመላከት ተማሪዎች ማህበራዊና ስሜታዊ የመማር ብልሃታቸውን አዳብረው የመማር ቁርጠኝነትና ስኬታማነት ማግኘት እንደሚችሉ ነው ፡፡ የማንበብ ሂደት መልዕክት ለማስተላለፍ በፀሐፊውና በአንባቢው መካከል የሚደረግ መስተጋብር ቢሆንም ተማሪዎች ንባብን በምን አይነት ብልሃት ተጠቅመው ቢያነቡ ችሎታቸው ሊዳብር ይችላል? የሚለው መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ሩትማን (1994) እና ወይንሸት (2007) በጥናታቸው እንደሚያመለክቱት ውስጣዊ ተነሳሽነት ኖሯቸው በራሳቸው ፈቃድ ብቻ ተመርተው የማንበብ ልምድ ያላቸው ተማሪዎች የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚችሉ ይገልፃሉ፡፡ በመቀጠልም በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የሚደርግ ንባብ የማንበብ ፍላጎትን ከመጨመሩና የአንባቢውን ችሎታ ከማሳደጉ ባሻጋር የቃላት ችሎታን፣ የስነ ፍቺን ችሎታና አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ያዳብርላቸዋል በማለት ዲክና ካትብሌን (1991) ደጋግመው ያስረዳሉ፡፡ ማንበብ የተፃፈን ነገር አንብቦ በጽሑፍ ዙሪያ ያለውን መልዕክት ከጠቀሜታው ጋር አገናዝቦ ትርጉም ሊሰጥ በሚችል መንገድ የሚደርግ ክሂል ነው፡፡ በመሆኑም በእነ ጉድማን (1994)፣ እና ሰሚዝ (1985) በአሜሪካ የተካሄደው ጥናት እንደሚያመለክተው ሁልጊዜ የሚያነቡ ተማሪዎች በንባብ ችሎታችው ደካማ እንኳን ቢባሉም ያለማቋረጥ ከማንበባቸው የተነሳ በተደጋጋሚ ከማያነበት ነገር ግን ጠንካራ አንባብያን ተብለው ከሚታወቁት የተሻለ ችሎታ እንደሚኖራቸው ይታምናል፡፡ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሊዳብር የሚችለው የተነበበውን ለመረዳት የሚያግዙ አቀራረቦችን አስቀደሞ በመተግበር ሲሆን አቀራረቦቹም፤ (ሀ) ቋንቋ ተኮር አቀራረብ ማለትም ተፈጥራዊ

በሆነ ዘዴ እንዲያነቡ የሚደረግበት፤ (ለ) ክሂል ተኮር አቀራረብ የማንበብ ክሂልን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ ፋይዳ ያለውና በተለይም በሁለተኛ ቋንቋ ላይ የሚተገበር፤ እና (ሐ) የስሜት ህዋሳትን ያቀናጀ አቀራረብ ሲሆን ይኸውም እዝናዊ፣ ዳሰሳዊና ተግባራዊ በሆነ የስሜት ህዋሳት አማካይነት የሚተገበሩ የሚሉት ናቸው።

ከላይ በተጠቀሱት የምሁራን ጥናቶች ላይ በመመርኮዝ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተለይም አጥኚዋ በምታስተርበት ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ዘንድ ማህበር ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ መርዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ያህል ነው? የሚለውን ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ምንም እንኳን ባጥኚዋ ርዕስ ዙሪያ የተካሔዱ በርካታ አገር በቀል ጥናቶችን የማግኘትና የማየት ዕድል ባይገጥማትም በተለይም በወይንሸት (2007) የተካሄደውንና በተዛማጅ ሁኔታ በከበደ (1999) እና በበላይነሽ (2002) የተደረጉ ጥናቶችን ለመቃኘት ሞክራለች። ይሁን እንጂ ከወይንሸት (2007) ጥናት በስተቀር ሌሎቹ በአብዛኛው በመማር ብልሃት ዙሪያ ላይ ብቻ ያተኮሩ ሆነው ተገኝተዋል። በሌላ በኩል የወይንሸት ጥናት ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ከአንብቦ መርዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ በሚለው ስር ከተማሪዎች የማንበብ ፍለጎት አኳያ ለማየት ችላለች። ይሁን እንጂ አጥኚዋ ከረጂም ዓመታት የማስተማር ልምዷ ካገኘችው ተሞክሮ አንፃር በምታሰተምርበት ትምህርት ቤት የሚገኙ የኦሮምኛ ቋንቋ አፈፊት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን ለማንበብ በሚያደርባቸው ጭንቀትና መረበሽ የሚታይባቸው፤ እርስበርስ የመረዳዳት ባህላቸው ዝቅተኛ መሆኑ፤ በ2ኛ ቋንቋ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ የሚቸገሩና ራሳቸውን የማበረታታት ብልሃት የሚጎላቸው ሲሆን በዚህም የተነሳ ላለማንበብ የሚያደርጉት ሽሽት ከፈተኛ ነው ። በመሆኑ ጥናቱን ለማካሔድ ለአጥኚዋ ተጨማሪ ምክንያት ሆኖታል።

በዚህም መሰርት ይህ ጥናት የሚከተሉትን ሁለት ጥያቄዎች ለመመለስ ሲባል ተካሂዷል።

1. ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል?
2. ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳች ችሎታ ለመተንበይ ያለው ድርሻ ምን ያህል ነው?

## 1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በማህበረ ስሜታዊ ብልሃትና በተማሪዋች አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረት ጥናቱ የሚከተሉት ሁለት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

1. ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል መመርመር፣
2. ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመተንበይ ያለው ድርሻ ምን ያህል እንደሆነ መፈተሽ፣

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

መምህራን በማስተማር ሂደት ልምድ እንዲሆን ማድረግ ያለባቸው ተማሪዎች ከፍርሃትና ከስጋት ነፃ ሆነው ከሌሎች ጋር በሰላም ተባብሮ የመማር ድፍረትን እንዲያዳብሩ የተማሪዎችን አቅም በየጊዜው በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ ድርሻ እንዳለባቸው ክራል (1994) ይገልፃሉ፡፡ ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ከማስገኘት አንፃር አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡

1. የቋንቋ መምህራን ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለውን ጠቀሜታ መምህራን ተገንዝበው እንዲጠቀሙበት ያግዛል፡፡
2. የሚመለከታችው ከፍተኛ የትምህርት ባለሙያዎች በርዕሱ ዙሪያ ተከታታይ አውደ ጥናቶች ስለሚኖራችው፣ አጫጭር ስልጠናዎች በማዘጋጀት ለመምህራን ሙያዊ ድጋፍ እንዲያደርጉ ያግዛል፡፡
3. ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት አንብቦ ለመረዳት ችሎታ በመጠቀም ረገድ ተማሪዎች ያላቸውን አመለካከትና ፍርሃት መንስኤውን ለማወቅ ይረዳል፡፡
4. በዚህ ርዕስ መነሻነት ሰፋ ያለ ጥናት ለሚያካሂዱ አጥኚዎች እንደ መነሻ በመሆን ያገለግላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ሸዋ ዞን በኢሉ-ገላን ወረዳ ውስጥ በኢጃጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ም የሚማሩ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ተካሂዷል፡፡ ጥናቱ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃት ጋር ምን አይነት ዝምንድና

እንዳለው ተፈትሿል። ነፃው ተላውጦ ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃቱ ሲሆን የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ደግሞ በጥገኛ ተላውጦነት ታይቷል።

## 1.6 የጥናቱ ውሱንነት

ይህ ጥናት የተካሄደው በገጠር ትምህርት ቤት በመሆኑ የተዛምዶው ውጤት ከከተማ ትምህርት ቤት ጋር በንጽጽር ለመመለከት አያስችልም። ለዚህም ዋነኛ ምክንያት የመኖሪያ አካባቢ በማህበረስሜታዊ የመማር ብልሃት አጠቃቀም ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩ ነገሮች አንዱ በመሆኑ ነው። በተጨማሪም የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት በመረጃነት ለመጠቀም እንዳያስችል በጥቅም ላይ የዋለው የአንብቦ መረዳት ተማሪዎች በብዛት የለመዷቸው እንጂ ሁሉንም የፈተና ዘዴዎች ባለማካተቱ የተማሪዊች ውጤት በተወሰነ ደረጃ ውስንነት ሊኖረው ይችላል።

## 1.7 የቁልፍ ቃላት ብያኔ

1. **ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት** (socio-affective strategy) ፤ ተማሪዎች የታላሚው ቋንቋ ተግባራት ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተረዳዱ እንዲሰሩ ግልፅ ያልሆነላቸውንም መምህሮራቻችውን እና በታላምው ቋንቋ ብቃት ያላቸውን ሰዎች እየጠየቁ እና ጭንቀታቸውን በመቀነስ የሚማሩበት ብልሃት ነው።
2. **አንብቦ የመረዳት ችሎታ** (Reading comprehension ablity) አንብቦ መረዳት ማለት ያነበቡትን ምንባብ እንዲሁ መቀበል ወይም አለመቀበል ሳይሆን ከዚህ በተለየ መልኩ ስለአነበቡት ምንባብ መጠየቅን፣ የምንባቡን አጠቃላይ እና ዝርዝር ሀሳብ መመርመርን፣ ማመዛዘንን እና ቀደም ሲል ካለ እውቀት ጋር ማመሳከርን የሚጠይቅ ተግባር ነው።

# ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. ቋንቋን የመማር ብልሃቶች ምንነት

የቋንቋ መማር ብልሃት ምንነትን ለመግለጽ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ እንደሌለ ፀሀፍት ያስረዳሉ ኢሊስ (1994)፡፡ በመሆኑም በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች (ሩቢን፣ 1987፤ ኦክስፎርድ፣ 1990፤ ኦማሌና ቻሞት፣ 1990) የራሳቸውን ብያኔ እንደሰጡ የኢሊስ (1994) ገለፃ ያስረዳል፡፡

እንደ ሩቢን (1987) ገለፃ የቋንቋ መማር ብልሃቶች ተማሪዎች የሚመሰሩትን የቋንቋ ስርአት ለማሳደግ የሚረዱና በቋንቋ መማር ላይ በቀጥታ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ብልሃቶች ናቸው፡፡ የኦማሊና ቻሞት (1990) ብያኔ የሚያሳየው ደግሞ የቋንቋ መማር ብልሃቶች የቋንቋ ተግባቦታዊ ችሎታን ንቁና በራስ የሚመራ ተሳትፎ ለማሳደግ የሚረዱ መሳሪያዎች መሆናቸውን፡፡

እንደ ኦክስፎርድ (1990) ገለፃ ደግሞ ቋንቋ የመማር ብልሃቶች ተማሪው የትምህርቱን ሂደት ቀላል፣ ፈጣን፣ ይበልጥ ማራኪና ምቹ፣ ራስ መርና ግልፅ ለማድረግ፣ ወደተሻለና አዲስ ክንውን ለመሻገር የሚወስዳቸው የተወሰኑ እርምጃዎች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ቋንቋን የመማር ብልሃቶች በተማሪዎች የሚተገበሩ፣ እውቀት ማካበትን ፣ ሀሳብ አስታውሶ መጠቀምን የሚያፋጥኑ የአሰራር ባህሪዎች፣ ተግባራዊ ደረጃዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ብልሃቶች ተማሪው የቋንቋ ትምህርቱን ሂደት ምቹ፣ ራስመርና አስደሳች በሆነ መንገድ ለመወጣት የሚያስችሉት መንገድ ነው፡፡

### 2.1.1 የቋንቋ መማር ብልሃቶች ንድፈ ሃሳብ

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በየዘመኑ በተለያዩ መስፈርቶች ላይ በመመስረት የቋንቋ መማር ብልሃቶችን ለመከፋፈል ተሞክሯል፡፡ በኢሊስ (1994) ብራውን (1994) እና ኦክስፎርድ (1990) የቋንቋ መማር ብልሃቶችን ከፋፍለው ለማሰየት ሞክረዋል፡፡ ክፍፍሎቹ ግን ከሞላ ጎደል በመሰረታዊ ሀሳብ ደረጃ ተመሣሣይ ማእቀፍ ያላቸው መሆኑን ኢሊስ (1994) ብራውን (1994) እና ዊሊያም እና በርደን (1997) ይገልፃሉ፡፡

ኢሊስ (1994) በሩቢን (1987) አከፋፈል መሰረት ተማሪዎች በቋንቋ መማር ወቅት የሚጠቀማቸው ሦስት አይነት ብልሃቶች እንዳሉ ተመላክቷል፡፡ እነዚህም ብልሃቶች የመማር ብልሃቶች ተግባቦታዊ ብልሃቶች ፣ ማህበራዊ ብልሃቶች ፣ ስሜታዊ ብልሃቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ብራውን (1994) እና ኤሊስ (1994) እንደሚገልፁት የቋንቋ መማር ብልሃቶች ሜታኮግኒትቪ፣ ኮግኒትቪ፣ ስሾዩ-አፌክትፍ በመባል በሦስት ምድቦች ይከፍላቸዋል፡፡

በዊሊያምስና በርደን (1997) እና በብራውን (1994) በተጠቀሰው በኦክስፎርድ (1990) አከፋፈል ደግሞ ቀጥተኛ እና ኢቀጥተኛ ያልሆኑ ስድስት የቋንቋ መማር ብልሃቶች እንዳሉ ተመላክቷል፡፡

ከላይ በቀረቡት አከፍፍል መካክል ኦክስፎርድ (1990) አክፋፋል ከሌሎች አከፋፋል የተሻለ ዝርዝር እንደሆነ በአልአክባሪና ሀያት ዘዲያ (2008) በተጠቀሰው ያሰረዳል፡፡ የዊሊያምስ በርዳን (1997) ሀሳብ የሚያሳየውም ይህንን የኦክስፎርድ (1990) አከፋፈል ከዚህ በፊት በነበሩት አከፋፈል የተካተቱ አብዛኞቹ ባህሪያት አጠቃሎ የያዘ እና የበለጠ ዝርዝር አከፋፈል መሆኑ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት የኦክስፎርድ (1990) ሞደል እና የብልሃት መጠይቅ ለቋንቋ መማር ብልሃቶች ምርምር መሰረት ሆኖ በማገልገል ላይ ያለ መሆኑን አልአክባሪ እና ሀያት ዘዲያ (2008) ይገልፃሉ፡፡ ኦክስፎርድ (1994)፣ ኢሊስ (1994) እና ዊሊያምስና በርደን (1997) የቋንቋ መማር ብልሃትን በሁለት ዋና ዋና ብልሃቶች ቀጥተኛ ብልሃት እና ኢቀጥተኛ ብልሃት ተብለው እንደሚከፍሉ የኦክስፎርድ (1990) አከፋፈልን ዋቢ በማድረግ ይገልፃሉ፡፡ ቀጥተኛ ብልሃት የሚባሉት የማስተዋል፣ አእምሮዊ፣ የማካካስ ብልሃት ናቸው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች የሚሰሩትን የቋንቋ ብልሃት በማሳደግ ረገድ ክፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ብልሃቶች እንደሆኑ የዊሊያምስና በርደን (1997) እንደሁም ብራውን (1994) ገለፃ ያመለክታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ብልሃቶች በቋንቋ መማር ወቅት በቀጥታ የሚተገበሩ እና ታላሚውን ቋንቋ መጠቀምን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ኢቀጥተኛ ብልሃት የሚባሉት ደግሞ የመገንዘቡ ወይም የመረዳት፣ ስሜታዊ፣ ማህበረዊ ብልሃቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ብልሃቶች መማርን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያግዙ ብልሃቶች ናቸው በማለት ዊሊያምስ  እና በርደን (1997)፣ብራወን (1994) ይገልፃሉ፡፡

ቋንቋ ማስተማር ማለት ተማሪው በተለያየ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብቶ ቋንቋውን እንዲማሩ ማድረግ ሲሆን ቋንቋን መማር ማለት ደግሞ ተማሪው ከመምህሩ ከሚያገኘው ዕውቀት በተጨማሪ ያካባቢውን ባህልና ዕሴት፣ ዕውቀትና ክህሎት ማወቅ ማለት ነው፡፡ ይሁንና ቋንቋን በመማር ረገድ እንቅፋት ሊሆኑ ከሚችሉ ጉደዮች ውስጥ መምህሩ ቋንቋን ሲያስተምር

የሚከተሉት የማስተማሪያ ዘዴ ምን አይነት ነው? ተማሪውስ በምን አይነት የመማር ብልሃት ቢማር ውጤታማ ሊሆን ይችላል? የሚል በርካታ ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡

ይሁን እንጂ ጥያቄዎቹን በአግባቡ ለመመለስ ከስነ ልቦና አኳያ መታየት ይገባቸዋል፡፡ በመሆኑም እንደ ስነልቦና ምሁራን ትንተና የሰው ልጅ ባህሪ ውስብስብ እንደመሆኑ ቋንቋን በመማር ረገድ የየግለሰቦች የማሰብ የማስታወስ፣ የመርሳት፣ የመፍርሃት፣ የመድፈር ወዘተ በሚል አእምሮአዊ ንቃት እየተመሩ የሚከናውን እንደመሆኑ መጠን ይኸውም ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት በዋናነት ሊጠቀስ እንደሚችል የዘርፉ ምሁራን ይገልፃሉ (ብራውን 2006)፡፡ ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት አስመልክቶ በ1990ዎቹ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ተማሪዎች ሊማሩ የሚገባቸው ፍዝ በሆነ መንገድ ሳይሆን ስሜታቸው ከውስጣቸው ፈንድቆና ፈንቅሎ በተጧጧፈ መንፈስ ተቀማጥሎ ሲወጣ ነው፡፡ ይኸውም ስሜታዊ ብልሃትን ያለማቋረጥ ተጠቅመው እንዲማሩ መምህሩ ከፍተኛ እገዛ ሊያደርግባቸው እንደሚገባ ሳክ (1997) ያሰረዳሉ፡፡

እንዲሁም ስሜታዊ የመማር ብልሃትን ከመጠቀም ጐን ለጐን ማህበራዊ ተግባቦትን ለመፍጥር፣ ከሌሎች ጋር በጋራ መተባበር አስፈላጊ በመሆኑ ያካባቢውን ማህበረሰብ ሀሳብና ባህል ለማወቅ ጥረት ማደረግና የሌሎችን ችግር ተጋግዞ መጋራት ለመማር ብልሃት ስኬታማነት ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ፓርክ እና ሌሎች (1997) ያሰረዳሉ፡፡ እንደምሁራን ገለፃም መማር እውን ሊሆን ከሚችልባቸው መንገዶች አንደኛው ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ሲሆን ይኸወም ተማሪዎች ማህበራዊ ብልሃትን ከራሳቸው ውስጣዊ ስሜት ጋር በማቀናጀት ከጥገኝነት መንፈስ ተላቀው ታላሚው ቋንቋ ሊያሟላ የሚችሉበት ብልሃት መሆኑን በትኩረት ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም የመማር ብልሃት ሲባል ቋሚነት የሌላው፤ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ሊለዋወጥ የሚችል የግለሰቦችን ወይም የቡድኖች እውነታ የያዘ ውስጣዊ ስሜትን አሟጦ መጠቀም የሚችል በራስ ማንነት በሚግለፀ ነፀብራቅነት ሌሎችን አክብሮ፣አፍቅሮ በጋራ የህይወት ግብን በዕለት ተዕለት ተግባር ለመተግበር የሚደረግ አስፈላጊ ብልሃት እንደሆነ ፓርክና ሌሎች (1997) አክለው ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም ይህ የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ብልሃት ከቀደሙት ብላሃቶች ተብለው ከተገለጹት መንገድ በጣም የተለየ ነው፡፡ ጠለቅም ያለ ሲሆን ከአራቱም የቋንቋ ክህሎች ጋርም ትስስር ያለው ሁኖ ከነዚህ አራቱ መካከልም በይበልጥ ትኩረትን የሰጠው በግንዛቤና በማስታወስ ትኩረትን በይበልጥ ይሰጣል፡፡ በመቀጠልም በተጠቀሱት ቃላት ዙሪያ ማብራሪያ ለመጥቀስ ያህል፤

- **ቋንቋ፤** ቋንቋ ስንል በሥራዓት የተሰደሩ ድምፆችን በወስጡ አካቶ የያዘ ሲሆን፤የሰው ልጅ ድምፃዊ መግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡
- **መማር፤** መማር ማለት ደግሞ ቀደም ሲል በነበረን ነገር ላይ ቢያንስ አንድ ነገር በአዲስ ነት መጨመርና ዕውቃታችን ማጎልበት ነው፡፡
- **ብልሃት፤** ብልሃት ስንልም አመጣጡ ከቀደሙት ግሪክ ቃል ሁኖ (ስትራቴጅ) ብልሃት ለሚለው ቃል ትርጉም በመሆን እየተገለገልንበት እንገኛለን፡፡

ይሁን እንጅ ወደ መማር ስንወስደው ደግሞ ተማሪዎች በሚማሩ ወቅት የሚያጋጥማቸውን ችግር ለማቃቀል፣ለመፍታትና ወደሌላ ነገር ለመሸጋገር የሚያስችላቸውን ነው፡፡ ስለዚህ ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ሦስቱም በተያያዘ መልኩ ሣይነጣጠሉ ሥራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ ተማሪው በትምህርቱ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ ይረዱታል፡፡

### 2.1.2 የቋንቋ መማር ብልሃቶች ባህሪያት

መማር ማህበራዊና ተግባቦታዊ በመሆኑ የተነሳ ሌሎችን ትምህርቶች ከመማር በርካታ መንገዶች እንደሚለይ ዊሊያምስና በርደን (1997) ያብራራሉ፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች እንደሚሉትም ቋንቋን መማር ከሌሎች ሰዎች ጋር ለመግባባት የሚከናውን በመሆኑ አእምሮአዊ ችሎታ ላይ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊና ተግባራዊ ክሂሎችም አስፈላጊ ናቸው፡፡

እንደ ኦክስፎርድ (1990) በዊሊያምስና በርደን (1997) እንደተጠቀሰው እነኚህ የቋንቋ ብልሃቶች ባህሪያትን ይዘረዝራሉ፡፡ እነሱም ተግባቦታዊ ችሎታን ለማጎልበት ማገዝ፤ችግሮቻችን በመፍታት ላይ ማተኮር፤ በተማሪዎች የሚተገበሩ ዉስን ተግባራት፤ ተማሪዎች በራስ እንዲተማመኑ መፍቀድ፤ አእምሮአዊ የሆነዉን ጉደይ ብቻ ሣይሆን ማንኛዉንም ዓይነት ማህበራዊ ስሜትና ተሳትፎን መጠየቅና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መማርን መደገፍ ናቸው፡፡

### 2.1.3 የማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ምንነት

የተለያዩ ሙሁራን ስለማህበረ ስሜታዊ ብልሃት የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ እንደ ሸንድግሪፍት (2003) ገለጻ ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት አንዱ የመማር ብልሃት ሲሆን ተማሪዎች እርስበርሳቸው እንዲረዳዱ፣ መረዳታቸውንም የምናረጋግጥበትና በተጨማሪም መረበሽን ለመቀነስ የሚጠቅም ስልት እንደሆነ ያስረዳል፡፡

በተጨማሪም Habite-Gabr, (2006) ገለጻ ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት በተፈጥሯቸው መደበኛ ትምህርት ያልሆኑ ነገር ግን በመምህሩና በተማሪው መካከል ጉልህ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት የሚፈጥር ብልሃት ነው፡፡

በሌላ በኩል እንደ ኦክሰስፎርድ (1990) ገለጻ ማህበረ ስሜታዊ ብልሃቶች አንድን ተማሪ ስለሚማረው ቋንቋ እንዴት ያለስሜት እንደሚሰማው እያስበ እና ከሌሎች ጋር እየተረዳዱ ሲማሩ ማህበረ ሰሜታዊ ብልሃቶትን ተጠቀመ እንላለን፡፡ ይህን ስልት እርስበርስ በመረዳዳት እና ያልተረዱትን ከሌሎች ወገን /ከጓደኛ/ ከመምህር፣ ከማህበረሰብ መጠየቅ የሚካሄድ የመማር ብልሃት ነው፡፡ በመተጋገዝ እና አብሮ በመሰራት የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታማ እንዲሆን ይናገራል፡፡ አክለውም ተማሪው ወይም መምህሩ ሊቀርፋቸው የሚገባቸው ስሜት ነክ ጉዳዩች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ምሳሌ፡ ጭንቀት፤ የናረ ጉጉትን፣ ፍርሃት፣ ቁጡነት፣ አለመረጋጋት፣ በሀሳብ አለመተማመን እና ሌሎችም እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ለሁለተኛ ቋንቋ መማር ሂደት ከፍተኛ ዋጋ እንዳላቸው ያብራራሉ፡፡

ይሁን እንጂ እንደ ብራውን (2002) ገለፃ የማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ተማሪዎችን በእርስበርስ ተራክቦ የሚያጋልጥ በመሆኑ ተማሪዎች በአከባቢያቸው ባለው ነገር ሁሉ መሳተፋቸው የቤተሰባዊነት፣ የጓደኛነት መንፍስ ስለሚሰማቸው ጎጂ ማህበረዊ እና ስሜታዊ ጉዳዩች ቦታ ያጣሉ፡፡ ስለሆነም እንደ ኦማይሊ እና ቻሞት (1990) ገለጻ አፍርሽ ስሜት ነክ ተለውጦዎችን መቆጣጠር የሚቻለው ከአቻ ጓደኛ ጋር በመረዳዳት ከሌሎች ጋር አዎንታዊ መስተጋብር በመፍጠር፣ የእርስበርስ ተሳታፊ እና ያልተረዱትን በማብራራት በመጠየቅ ከራስ ጋር በመነጋገር ራስን ማበረታታት እንደሆነ ይገልጻሉ ፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት የሚቻለው ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ይሁን በውጭ ቋንቋ መማር የተሻለ ውጤት የሚያሳዩት በክፍል ውስጥ ሁኔታ በመተጋገዝ እና አብሮ በመስራት ላይ በተመሰረተ መማር ሂደት ያለፉ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው የቤተሰብ፣ የአካባቢ፣ የክፍል ውስጥ ሁኔታ በተማሪዎች ውጤት ላይ በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ ማሳደር እንደሚችል ነው፡፡

## 2.1.4. የማህበረ ስሜታዊ ክፍሎች

አሊስ (1994) እና ሂስምናጉል (2000) እንደገለጹት ማህበረ ስሜታዊ ብልሀት በሩበን (1987) አከፋፈል መሰረት አንድ ተማሪ ስለሚማረው ትምህርት ያለውን ስሜት በመጠየቅ፣ በመተጋገዝ፣ ስሜታቸውን በመቆጣጠርና አብሮ በመስረት ላይ የተመሰረተ ብልህት እንደሆነ ገልጿል። በተጨማሪም አልአክባሪ እና ሀያት ዚያድሀ (2008) እና ታባይንግሉ (2003) ገለጻ ስሜታዊ ብልሀቶች በተማሪዎች ስሜት ላይ የሚያተኩሩ ሲሆኑ ከቋንቋው መማር ጋር የሚዛመዱ ውስጣዊ ስሜቶችን፣ መነሳሳቶችን፣ ፍላጎቶችን፣ ጭንቀትን ለመቆጣጠር የሚያግዙ ብልሀቶች ናቸው። ማህበራዊ ብልሀቶቸ ደግሞ የቋንቋ መማር መስተጋብርን በመፍጠር ክህሎት ማሳደግን የሚመለከትና ከሌሎች ጋር የሚኖርን መስተጋብር ለማፋጠን ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ ከሌሎች ጋር በትብብር መስራት እና ለሌሎች ሰዎች ሀሳብና ስሜት ግንዛቤ በመፍጠር የሚመለከት ናቸው።

በአጠቃላይ የማህበረ ስሜታዊ ንዑስ ብልሀቶች በርካታ ቢሆንም በዚህ ጥናት ትኩረት የተሰጠባቸው በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳላቸው በተለያዩ ጥናቶች የተገለፁት ነው። እንደ ኦክስፎርድ (1990) ገለጻ የማህበረ ስሜታዊ ብልሀት ንዑሳን ክፍሎች፣ ራስን ማበረታታት፣ጥያቄ መጠየቅ፣ በትብብር መስራት እና ጭንቀትን የመቀነስ ብልሀቶች ናቸው። እነዚህን ንዑሳን ክፍሎችም በቅደም ተከተል ቀጥሎ በዝርዝር ይቀርባሉ።

### 2.1.4.1 የመጠየቅ ብልሃት

ይህ ብልሃት ተማሪዎች ያልተረዱትን ሃሳብ መምህራንን ወይንም ጓደኞቻቸውን በመጠየቅ የሚገነዘቡበት ዘዴ ነው። ይህ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከሚያግዙ ብልሃቶች አንዱ ሲሆን የተለያዩ ዘዴዎችንም አካቷል። እነሱም ማብራሪያ መጠየቅና ማስተካከያ መጠየቅ ናቸው። ማብራሪያ የመጠየቅ ዘዴ ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ሂደት ውስጥ ለምሳሌ ያልገባቸውን አዳዲስ ቃላት ትርጉም ወይም አውዳዊ ፍቺ ከሎሎች ጓደኞቻቸው በመጠየቅና በመረዳዳት የሚማሩበት ስልት ነው። ማስተካከያ መጠየቅ ማለት ደግሞ ተማሪዎች በስህተት የተረዷቸውን ሃሳቦች ከጓድኞቻቸው ወይም ከመምህራቸው እርማት የሚወስዱበት ስልት ነው።

### 2.1.4.2 ራስን የማበረታታት ብልሃት

ይህ ብልሃት ከማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃት አንዱ ሲሆን ተማሪዎች ጥሩ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዲኖራቸው የሚያግዝ ብልሃት ነው። ራስን የማበረታታት ብልሃት ተማሪዎች ዓላማቸውን ለማሳካት እና የተሰጣቸውን ተግባር በአግባቡ ሰርተው እንዲያጠናቅቁ መነሳሳትን የሚፈጥርና ሀሳብ የማመንጨት አቅማቸውን እንዲጎለብት የሚያግዝ ብልሃት ነው። ስለዚህ ጥሩ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዲኖራቸው የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። እነሱም:- አወንታዊ አመለካከትን ማዳበር፣ ለመማር ዝግጁ መሆን እና ራስን መሸለም ናቸው። አወንታዊ አመለካከትን ማዳበር ሲባል ምንምእንኳ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደካማ ቢሆንም ለወደፊት ማሻሻል እንደሚችሉ ለራሳቸው አወንታዊ ግምት በመስጠት ራሳቸውን የሚያበረታቱበት ዘዴ ነው። ለመማር ዝግጁ መሆን ማለት ደግሞ በአንብቦ የመረዳት ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ስህተት ልሰራ እችላለሁ ከሚል ፍራቻ በመውጣት በራሳቸው የመተማመን አቅማቸውን የሚያሳድጉበት ነው። ሌላኛው ስልት ራስን መሸለም ሲሆን ይህ ዘዴ ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ሂደት ውስጥ በጓድኞቻቸው ወይም በመምህሮቻቸው የሚሰጣቸው ቃላዊ ወይም ቁሳዊ ሽልማት ነው። ይህም ማለት ተማሪዎች በራሳቸው መስራት እንደሚችሉ ራሳቸውን ማሳመን የሚችሉበት እና የሚያበረታቱበት ሲሆን በተመሳሳይ መምህሩም በተለያየ መንገድ ተማሪዎችን የሚያበረታታበት ዘዴ ነው።

### 2.1.4.3 በትብብር የመስራት ብልሃት

በትብብር የመስራት ብልሃት ምንነት አስመልክቶ የተለያዩ ምሁራን ብያኔዎችን ሰጥተዋል። ለአብነት ያክል እንደ ጆንሰን እና ጆንሰን ሞንሰን (1999) ገለጻ በትብብር የመማር ብልሃት የሚባለው ተማሪዎች አንድ ላይ በጋራ በመስራት የራሳቸውንና የሌሎችን መማር ሁኔታ የሚያሻሽሉበት እንደሆነ ሲገልፅ ሪክራጅስ እና ሮጀርስ (2003) ተማሪዎች በጋራ ሆነው የተሻለ ስራ ይሰሩ ዘንድ መምህሩ የተለያዩ የትብብራዊ መማሪያ ዘዴዎችን እያቀያየሩ መጠቀም እንዳለበት ያስገነዝባሉ። ሳለቪን (1999) ሲገልፁ በትብብር የመማር ብልሃት የተለያየ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች በትንሽ ቡድን በማቀናጀት እርስበርስ በመበረታታት አብረው የሚሰሩበት እንደሆነ ገልጸዋል። ሪታራኒ (2009) በበኩላቸው በትብብር የመማር ብልሃት ከማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ ሲሆን በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች አብረው ሰርተው የጋራ የሆነ አጥጋቢ ምላሽ የሚያገኙበት ነው። ጥሩ የሆነ ስራ ከስሩ በጋራ የሚሸለሙበት ከተጠበቀው በታች ከስሩ ደግሞ የሚቆጩበት ነው ይላሉ። አያይዘውም ያለውን ጠቀሜታ ሲገልፁ

የሚማሩበት የትምህርት ይዘት እንዲገነዘቡ ያነቃቃቸዋል እርስ በርስ ተወዳዳሪ መንፈስ ተገላልፀው በመተሳሰብ ለጋራ ጥቅም በጋራ ይሰራሉ፡፡

በትብብር መማር ተማሪዎች ማህበራዊ ክህሎቶቻቸውን የሚያሳድጉበት የእርሰ በርስ የመረዳዳት መንፈስ በማዳበር በቡድናቸው ውስጥ አዎንታዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ ይህን አስመልክተው ጆንሰን እና ጆንሰን ሞንሰን (2012) እንዳስቀመጡት በትብብር የመማር ብልሃት በአዲስ የማስተማሪያ ዘዴ ውስጥ ተማሪዎች ያላቸውን እውቀት በንቃት እንዲገነዘቡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ነው፡፡ እንዲሁም መማር ማህበራዊ እንደመሆኑ መጠን ተግባሩን ለመፈፀም ተማሪዎች በትብብር እንዲሰሩ በማድረግ የእረሰበርስ ግንኙነታቸውን አዎንታዊ እንዲሆን፣ ችሎታቸውን፣ ብቃታቸውን በማሳደግ ተፈጥሮ ባደለቻቸው ስጦታ ላይ እንዲነሳሱ የሚያደርግ ነው ብለዋል ናይት (1990) እንደገለፁት በትብብር መማር ተግባር ከመምህራን ይልቅ በተማሪዎች በበላይነት የሚከናወን ሲሆን ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እየተማማሩ የቀረበውን ትምህርት ይዘት ይሸፍናሉ፡፡ በዚህ ወቅት ጠቃሚ የሆነውን ማህበራዊ ክህሎቶቻቸውን እያሳደጉ ይሄዳሉ፡፡

የተለያዩ ምሁራን በትብብር የመማር ብልሃት ጠቀሜታን ገልጸዋል፡፡ እንደ ሪታራኒ (2009) ገለጻ በትብብር የመማር ብልሃት የተማሪዎችን በጥልቀት የማሰብ አቅማቸውን ያጎለብታል፣ አካባቢን በደንብ ለመረዳት ያስችላል፣ የደካማ ተማሪዎችንም አቅም ከፍ ያደርጋል፣ እንደ አንድ የመማሪያ ዘዴ አማራጭ በመሆን ያገለግላል ይላሉ፡፡ ሪቻርድ እና ሬነደይ (2002) የተለያዩ ጥናቶችን በመጥቀስ በትብብር የመማር ብልሃት ያለውን ፋይዳ ሲያስቀምጡ ተማሪዎች የተለያዩ ሀሳቦችን እንዲያመነጩ፣ ዘና ብለው መወያየት እንዲችሉ ማድረግ፣ ችግሮችን ተወያይተው እንዲፈቱ ማስቻል፣ ጥልቅ የሆነ የመስራት ፍላጎት እንዲኖራቸው እና በአጭር ጊዜ እየተነጋገሩ ብዙ ጥያቄዎችን መስራት ይችላሉ ብለዋል፡፡ በተጨማሪም ጆንሰን እና ጆንሰን ሞንሰን (2009) በትብብር መማር ጊዜ ተማሪዎች የተለዩ አመለካከቶችን እንዲቀበሉ የሌሎችን ሀሳብና ስሜት በጥልቀት እንዲረዱ ሌሎችንም ሁኔታዎችን ለማወቅ ፍላጎት ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራኖቹ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው በትብብር የመማር ብልሃት ተማሪዎች እርስበርስ በመተጋገዝ፣ በመረዳዳት እንዲማሩ የሚያደርግ ስኬታማ የማስተማሪያ ዘዴ እንደሆነና በተጨማሪም በትብብር መማር ወቅት ተማሪዎች የተለየዩ ተግባራትን እርስበርስ በመረዳዳት እና በመደጋገፍ የራሳቸውን መማር ሁኔታ በማሳደግ የሌሎችም እንዲያድግ

ማድረግ የአስተሳሰብ አድማሳቸውንና ማህበራዊ ክሂሎታቸውን የሚሳድግ ወይም የሚያጎለብት መሆኑን ነው፡፡

### 2.1.4.4 ጭንቀት የመቀነስ ብልሃት

ጭንቀት የሰውልጅ አንዱ የተለመደ የህይወት አካል ነው፡፡ ነገርግን የአንዳንድ ሰዎችን ህይወት በእጅጉ ሲጎዳ ይስተዋላል፡፡ ምሁራኖች እንደሚያስረዱት በእርግጥ ጭንቀት አስፈሪ ቢሆንም የመጨነቅ ደረጃውን ለመቀነስ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ ከስልቶቹም መካከል በጥልቅ መተንፈስ፣ አሉታዊ አመለካከቶችን ማስወገድ፣ ፍራቻን ማስወገድና እገዛን መጠየቅ ናቸው፡፡ (ባላንዲኒ ኤም. ፌካሮታ፣ 2017)፡፡ እንደምሁራኑ ገለጻ በጥልቅ መተንፈስ ሲባል የአተነፋፈስ ስርአታችን ማስተካከል ማለት ነው፡፡ ብዙ ሰዎች በተጨነቁ ወቅት ስለአተነፋፈሳቸው ብዙም ትኩረት አይሰጡም በዚህም የተነሳ የአተነፋፈስ ስርአታቸው ያልተስተካከለ ይሆናል ስለሆነም ይህ የአተነፋፈስ ስርአት ደግሞ በአእምሯችን የፍርሃትና የጭንቀት ስሜታቸውን ከፍ ያደርገዋል፡፡ ነገርግን የአተነፋፈስ ስርአታችንን በዝግታ ካደረግን የመጨነቅ ስሜታችንን መቀነስ እነደሚችል ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡

## 2.2. የማህበረ ስሜታዊ ብልሃትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ንድፈ ሃሳባዊ መሰረት

ተማሪዎች ቋንቋን ለመማር ሲመጡ በቋንቋ ትምህርታቸው ላይ ወሳኝ የሆኑ አወንታዊ እና አሉታዊ ተጽእኖዎች ማሳደር የሚችሉ የየራሳቸው ግላዊ ባህርያት፣ ክሂል፣ የመማር ብልሃትና ግብ ይዘው ነው፡፡ (ሪቻረድስ 1985) ፡፡ በዚህም ምክንያት በተማሪዎች መካከል የመማር ብልሃት ልዩነት መፈጠሩ የማይቀር ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ የሁሉንም ተማሪዎች ፍላጎትና ግብ ለማሳካት የተለያዩ ብልሃቶችን መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል (ፊደልማን 2000) ፡፡

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በተለያዩ ጊዜያት የመማር ብልሃትና አንብቦ መረዳትን በተመለከተ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ጥናቶቹም እንደሚያመለክቱት ተማሪዎች ባላቸው ተፈጥሯዊ ባህሪ፣ የአካባቢ ልዩነት ተጽእኖዎች ምክንያት የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው እንዴት ማዳበር እንደሚችሉ አመልክተዋል (ብሎክ፣ 1992) ፡፡

ግራቤና ስቶለር (2002) በጥናታቸው እንደገለጹት ቀደም ባለው ዘመናት ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ለአንብቦ የመረዳት ችሎታ መጎልበት ምንም ዓይነት ሚና እንደሌለው ነበር

የሚታየው። ሆኖም ግን ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በተደረጉ ጥናቶች ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ለአንብቦ መረዳት ችሎታ መጎልበት ትልቅ ሚና እንዳለው ጥናቶች አመላክተዋል።

ባኦከይ (2012) ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን በማሻሻል ረገድ ያለውሚና በዩኒቨረስቲ ተማሪዎች ላይ ያካሄደው ጥናት እንደሚያሳየው በየኒቨርስቲ ያሉ ተማሪዎች አንብበው እንዲረዱና በጥልቀት እንዲያውቁ እንዲገመግሙና መረጃን እንዲያደራጁ ይሁን እንጂ በዩኒቨርስቲው የሚማሩ የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችግር እንዳለባቸው ጥናቱ ያመለክታል። ይህም የሆነበት ምክንያት የተማሪዎች ዝቅተኛ የሆነ የማንበብ ፍላጎት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የማንበብ ብቃት ማነስ እንደ ምክንያት ተጠቅሷል። ይህን ችግር ለመቅረፍ ማህበረ ስሜታዊ ብልሃትን በማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማሻሻል ጥናት ተደርጓል። የጥናቱ ውጤትም ያመላከተው ማህበረ ስሜታዊ ብልሃትን ተግባራዊ መደረጉ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ መሻሻል መቻሉን ነው።

## 2.3. አንብቦ የመረዳት ምንነት

ንባብ የጊዜ ርዝመት ላራራቃቸው ትውልዶች በቅርበት ተገናኝተው የቃል በቃል ተግባቦት ለማያደርጉ ሰዎች ንግግርን ወክሎ መልእክት የሚደርስበት ወይም የሚዳረስበት ብልሃት ነው። ማንበብ ማለት ደግሞ የቀደመ ዕውቀትን ተጠቅሞ በጽሑፍ ላይ የሰፈረ ሀሳብን አንብቦ በትኩረት መልዕክቱን መረዳት ወይም መቀበል ማለት ነው። በሌላ አገላለፅ አንብቦ መረዳት ማለት አንድ ሰው ሰላነበበው ነገር በቂ ግንዛቤ የሚይዝበት ክስተት ሲሆን የመጨረሻ ግቡም ያነበቡትን የጽሑፍ መልዕክት በተሟላ ሁኔታ መረዳት ማለት ነው። ይኸውም አንባቢው ባነበበው ርዕስ ጉዳይ ላይ የጽሑፍን ዋና ዝርዝር ሀሳቦችን በመለየት ትርጉም ወይም ስሜት እንዲፈጥርበት በማድረግ ተገቢና ትክክለኛ ማጠቃለያ ወይም መደምደሚያ ላይ መድረስ ሲችል እንደሆነ እንድሪስ (2000) ያስረዳሉ።

በሌላ በኩል አንብቦ መረዳት ማለት በፅሁፍ ውስጥ ሊተላለፍ የሚፈለገውን መልዕክት የመገንዘብ ሂደት ነው። ተስፋዬ (1986) ሲያስረዱ አንብቦ መረዳት ማለት ያነበቡትን ምንባብ እንዲሁ መቀበል ወይም አለመቀበል ሳይሆን ከዚህ በተለየ መልኩ ስለአነበቡት ምንባብ መጠየቅን፣ የምንባቡን አጠቃላይ እና ዝርዝር ሀሳብ መመርመርን፣ ማመዛዘንን እና ቀደም ሲል ካለ እውቀት ጋር ማመሰካከርን የሚጠይቅ ተግባር ነው በማለት ይገልፁታል። ቶንጄስ (1991) እንደሚገልጹት፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝርዝር ሀሳቦችን መለየት፣ ዋና ሀሳቦችን

መለየት፣ ሂደቱን መገመት፣ በንፅፅር መተንበይ፣ የምክንያት እና ውጤትን ግንኙነት መገመት፣ የገጸባህሪያትን ባህሪ መገመት፣ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት፣ ዘይቤያዊ አገላለጾችን መተርጎም እና የመሳሰሉትን ተግባራትን ማከናወንን ይጠይቃል፡፡ እንዲሁም አንድን አሀድ በሚገባ አንብቦ በወጉ ለመረዳት የሚከተሉትን ዘጠኝ ተግባራት ማከናወን እንደሚያስፈልግ ቶንጀስ (1991) ይገልጻሉ፡፡ ተግባራቱም የንባብን ዓላማ መረዳት፣ እንደ ንባቡ ዓላማ የንባብ ስልትን መለዋወጥ፣ ከምንባቡ ጠቃሚ መረጃዎችን መለየት፣ የምንባቡን ተጠያቂያዊ አወቃቀር መገንዘብ፣ አዳዲስ መረጃዎችን ከቀዳሚው እውቀት ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ መለየት፣ ለአገባባዊና ለስነ-ፍቻዊ ባህሪያት ትኩረት መስጠት፣ አሀዱን ከግልፅነት፣ ከምሉዕነት፣ ከወጥነት አንጻር መገምገም፣ አንብቦ መረዳት አለመቻል ችግሩ ምን እንደሆነ መለየትና አሀዶችን እንዴት መረዳት እንደሚቻል መወሰን፣ ከሚሉት ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው አንድን ፅሁፍ አንብቦ መልዕክቱን በተገቢው መንገድ ለመረዳት የተለያዩ ክንዋኔዎችን ማከናወን አስፈላጊ መሆኑ ነው፡፡ እነዚህም ክንዋኔዎች ደረጃ በደረጃ የሚከናወኑ ሂደቶች ናቸው፡፡

ግሪሌት (1981) በበኩላቸው አንብቦ መረዳት ማለት ከፅሁፍ ውስጥ የተፈለገውን ሀሳብ በተቻለ መጠን በብቃት ማውጣት ነው ይላሉ፡፡ ይህም የሚያሳየው ተማሪው ምንባቡን የሚያነብበትን ዓላማ ተረድቶ የተጠየቀውን ሀሳብ ከተገነዘበ አንብቦ መረዳቱን ያመለክታል ማለት ነው፡፡ ናታል (1996) ደግሞ አንብቦ በመረዳት ሂደት የአረፍተ ነገሮች አቀነባበር ለምሳሌ አንድ አረፍተ ነገር ከቀድመው ወይም ከተከተለው አረፍተ ነገር ጋር ያለውን ግንኙነትና ግጥምጥምነትን የሚፈጥሩ አያያዦች እና የፀሀፊው ሀሳብ የሚንጸባረቅባቸው በመሆኑ ዋና ተተኳሪዎች ናቸው ብለዋል፡፡ ስለሆነም አንብቦ መረዳት የሚለው እሳቤ የፅሁፍን ፍሰት መረዳትንም የሚገልጽ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ማሪው (1998) እንደሚያስረዱት በተማሪዎች ዘንድ ከአንብቦ መረዳት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችግሮችን ለማስወገድ የሚነበበው ጽሁፍ ምን አይነት ነው? የማነበበው ለምን አላማ ነው? የማነበው እንዴት ባለስልት ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች መመለስ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም ተማሪዎች ወይም አንባቢዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን ማስተካከል ይችላሉ፡፡

ሺንግ (2000) አንብቦ መረዳት የአንድን ፅሁፍ ሀሳብ መረዳትን፣ መጨበጥን የሚገልጽ እሳቤ እንደሆነና የፀሀፊውን ሀሳብ ውይም መልዕክት መለየት፣ አውዳዊ ፍቺዎችን መገንዘብና ከአውድ ውጪ የሆኑ ፍቺዎችን መረዳትንም የሚያጠቃልል መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ስለሆነም

አንብቦ የመረዳት ሂደት አንድ ፀሀፊ በፅሁፍ ለማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት በብቃት መረዳት መቻልን የሚያመለክት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሺንግ አንብቦ የመረዳት ተግባርን በሁለት ከፋፍሎ ይገልጸዋል፡፡ በመጀመሪያ የሚያቀርበውም በምንባቡ ውስጥ በግልጽ የተቀመጡ ሀሳቦችን አንብቦ መረዳትን ነው፡፡ በዚህ ስር በፅሁፍ ውስጥ የቀረቡትን ዋና ዋና ሀሳቦችን መገንዘብን፣ በግልጽ የተቀመጡ ሁነቶችን (events)፣ ድርጊቶችን፣ ክስተቶችን ወዘተ. ቅደምተከተል ማስታወስን፣ በፅሁፍ ውስጥ በግልጽ የተቀመጡ ተመሳሳዮችን እና ልዩነቶችን መለየትን፣ የምክንያት እና ውጤት ትስስርን ማስታወስን ወዘተ. ገልጸዋል፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች ተጠየቃዊ ዕውቀትንና ግምትን በመጠቀም በምንባቡ ውስጥ በግልፅ ያልተቀመጡ ሀሳቦችን አንብበው የሚረዱበትን ሁኔታ ጠቁሟል፡፡ ይህ አይነት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደግሞ ካሉት መረጃዎች በመነሳት የምንባቡን ሀሳብ መለየትን፣ ፍሬሀሳቡን (ጭብጡን) መለየትን፣ ከምክንያት እና ውጤት ትስስር የተነሳ ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን ነገር መገመትን፣ በፅሁፍ ውስጥ በግልፅ የተቀመጠውን ፍንጭ በመጠቀም የገፀባህሪያትን ባህርይ መገንዘብን፣ ፀሀፊው የተጠቀመበትን ቋንቋ ፍቺ መለየትን ወዘተ. የሚመለከት ነው፡፡

ዌነርና ባዝማን (1997) እንደሚያስረዱት ደግሞ፣ ንባብን መማር ነጠላ ክሂልን መማር አይደለም፡፡ ነገር ግን የተለያዩ ክሂሎችን መማር ነው፡፡ ምክንያቱም የቋንቋ ክሂሎች እርስበርሳቸው የተያያዙ ስለሆነ አንዱን ክሂል በምንማርበት ጊዜ ሌሎች ክሂሎችም በተጓዳኝ ይቀርባሉ፡፡ በየጊዜው በሚደረገው አንድን ክሂል የማዳበር ሂደት ሌሎች ክሂሎችም እየዳበሩ ይሄዳሉ፡፡ ለምሳሌ የቃላት ዕውቀት በተሻሻለ ቁጥር አንብቦ የመረዳት ችሎታ ይሻሻላል፡፡ አንብቦ ለመረዳት በሚደረገው ሂደትም የአዳዲስ ቃላት ፍቺን መረዳት ይቻላል፡፡ ምሁራኑ አክለውም እንደሚገልጹትም በተገቢው መንገድ አንብቦ ለመረዳት በቂ የቃላት ዕውቀት ያስፈልጋል፡፡ በቂ የቃላት ዕውቀት ለማግኘት ደግሞ በስፋት ማንበብ ያስፈልጋል፡፡ የቃላት ዕውቀትና አንብቦ መረዳት በእጅጉ የተቆራኙ በመሆናቸው የቃላት ዕውቀት ሲዳብር አንብቦ የመረዳት ችሎታም ይዳብራል፡፡ ብዙ በማንበብም የቃላት ዕውቀት ይሰፋል፡፡ በሌላ በኩል ስሚዝ (1985) እደሚገልጹት አንብቦ መረዳት አንባቢ ይዞት ለሚነሳው ጥያቄ መልስ ማግኘት ማለት ነው፡፡ የሚነበብን ፅሁፍ አሰመልክቶ ጥያቄ መጠየቅ አንብቦ የመረዳት ትምህርት ባህሪ ነው፡፡ አንባቢ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ አገኘ ማለት በአንባቢውና በፀሀፊው መካከል ተግባቦት መኖሩን ያሳያል፡፡ በፅሁፉ እና በአንባቢው መካከል ተግባቦት አለ ለማለት የሚቻለው መረዳት ሲኖር

ነው። ስለሆነም አንብቦ መረዳትን እና ተግባቦትን መለያየት አይቻልም ማለት ነው። ባጭሩ አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ ፅሁፍ ውስጥ የሚፈለገውን መረጃ ለይቶ ማውጣት መቻል ነው

### 2.3.1. አንብቦ የመረዳት ብልሃቶች

የማንበብ ችሎታ በእርጋታና በማሰተዋል አንብቦ በተነበው ርዕስ ዙሪያ ግልጽ ግንዛቤ የመረዳት ችሎታ ነው። በመሆኑም ጥሩ አንባብያን የሚባሉት ያነበቡትን በሚገባ የሚረዱና ባነበቡትም የሚደሰቱ ናቸው። ይሁንእንጂ ጥሩ አንባቢ ለመሆን የማንበቢያ ብልሃትን መጠቀም እጅግ አስፈላጊ መሆኑን የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ።

የማንበብ ብልሃቶች የተሻለ አንባቢ ሆኖ ለመብቃት የሚያግዙ ፍንጮች ወይም ቴክኮች ናቸው። በመሆኑም በራስ ተማምኖ ራስን በራስ ተቆጣጥሮ ከቴክስቱ ጋር መስተጋብር ፈጥሮ ለማንበብ ያስችላሉ። በለሌ በኩል የማንበብ ብልትሃቶች ከንባብ በፊት በንባብ ጊዜ እና በኋላ ሊተገበሩ የሚችሉ ናቸው (ብራውን፣ 2006) ።

**ቅድመንባብ፤** ማንበብ ከመጀመር በፊት በየትኛው የቅድመንበብ ብልሃት መጠቀም እንደሚበጅ ማቀድና ራስን መቆጣጠር፤ ቀጥሎም ስለ ሚነበበው ቴክስት ይዘት መገመት፤ ቀዳሚ ዕውቀትን ተጠቀሞ መተንበይ ለምን እንደሚነበብ መወሰን መጠየቅ በሚነበበው ዙሪያ የቁልፍ ቃላትን ትርጉም መገመት ቴክስት ማዘጋጀትና በቂ ግንዛቤ መያዝ የሚቻልበት የማንበብ የመጀመሪያ ደረጃ ነው። እንደ ሳናው (2002) አባባል የቅድመንባብ ተግባራት አንብቦ ለመረዳት የማይጠቀም ብልሃት ከሆነ አንባቢው ትክክለኛ ጊዜውን ተጠቅሞ እንዳያነብ ያደርጋል። ይህም ማለት መምህራን የቅድመንባብ ትንበያ ጥያቄዎችን ጠይቀው ራሳቸው ደግሞ መልሱን የሚሰጡ ከሆነ ተማሪዎች የማንበብ ፍላጐት አይኖራቸውም። በአንፃሩ ጥሩ ሆነው የተዘጋጁ የቅድመንባብ ተግባራት ለተማሪዎች ከዳራዊ ዕውቀታቸው ጋር የሚነበበውን ነገር እንዲያዛምዱ ዕድል ስለሚሰጣቸው የማንበብ ፍላጐት ያሳድርባቸዋል።

**በንባብ ጊዜ፤** በንባብ ወቅት ስለሁነቱ፣ ስለትንበያው ምን ሊከተል እንደሚችል እየገመቱ ማንበብ ሲሆን አልፎ አልፎም ቆም እያሉ በሚነበበው ርዕስ ዙሪያ ግንዛቤን የማረጋገጥ፤ ዋና ሀሳብና ዝርዝር መረጃዎችን ለማገኘት የሚያስችልና ከቅደመ ንባብ ተግባራት የላቀ እንደሆነ ሳናው (2002) ያስረዳሉ።

ድህረንባብ፣ የትንበያውን ትክክለኛነት ከተነበበው ቴክስት ይዘት አንፃር ማረጋገጥ፣ በመቀጠልም በተነበበው ጽሑፍ ዙሪያ ቻርት አዘጋጅቶ የማላውቀውን ነገር ለማወቅ የምሻው፣ ያወኩት በማለት የተገኘውን መረጃ መመዝገብ ነው፡፡

የማንበብ ብልሃት እውን ለማድረግን የተነበበውን ነገር ፋይደውን መወሰን ደስተኛ ግንኙነት መፍጠር ጣልቃ ገብ ግምት መስጠት፣ መጠየቅ፣ ጥያቄውን መፃፍ፣ ቀጥሎም በግል መልስ መስጠት እና በመጨረሻም ምናባዊ ግንዛቤን እውን አድርጎ ጭብጡን ለይቶ በመግለፅ ሁነት አንድ፣ ሁነት ሁለት፣ ሁነት ሶስት ወዘተ በማለት ምክንያትና ውጤቱን መግለፅ የሚሉ መሆናቸውን ብራውን (2006) ገልጿል፡፡

## 2.4. አንብቦ ለመረዳት የጥሩ አንባቢ ባህርያት

አንብቦ ለማረዳት ያለፈ ልምደን ከመጠቀም በተጨማሪ የቃላት ዳራዊ ዕውቀት መዳበር፣ የቃላትን ፍቺ (ትርጉም) ማወቅ፣ አከባቢያዊና ማህበራዊ ልማዶችን፣ ማህበራዊ ግንኙነትና ማህበረ ኢኮኖምያዊ ሁኔታን የመማሪያ ክፍል ጓደኛ፣ ቤተሰብ ወዘተ የጐላ ድርሻ አላቸው፡፡ በመሆኑም አንብቦ መረዳትን ለማዳበር እና አዳዲስ ብልሃቶችን ለማስተዋወቅ ቀጥተኛ የማስተማሪያ ዘዴ ውጤታማ ሲሆን በዚህ ዘዴ ስርም የሚከተሉትን አራት የማንበብ ብልሃቶች መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ አቀላጥፎ ማንበብና ለፍጥነቱ የልኬት ደረጃ መስጠት (Accuracy and Rate)፣ በትክክለኛ የድምፅ አወጣጥ ማንበብ (Intonation) ፣ የፊት ገፅታን በመለዋወጥ ስሜትን በሚነካ አገላለፅ ማንበብ (Expression) እና ቃላትን በተገቢ ሁኔታ እያጠሩ ማንበብ (phrasing) የሚሉ መሆናቸውን ብራውን (2006) ያስረዳል፡፡

አንብቦ የመረዳት ብልሃት አጠቃቀምን አስመልክቶ የማህበረ ስሜታዊ ብልሃትን አስፈላጊነት (ብራውን 2006፣ 108) የሚከተለውን ይላል፡፡


ተማሪዎች በማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ተጠቅመው በራስመር በሚያነቡበት ጊዜ በመጀመሪያ ውስጠ ህሊናቸውን ይነካቸዋል፣ ቀጥሎም ያነቃቃቸዋል፣ ቆይቶም ስለአነበቡት ታሪክ እንዲያሰቡ ያስገድዳቸዋል፣ እንደገናም መልሰው መለልስው እንዲያነቡ ይገፋፋቸዋል፣ እንዲያሰቡ፣ እንዲመራመሩ፣ እንዲጠይቁ፣ ያነበቡትን ሀሳብ ለሌላ እንዲያካፍሉ፣ ያዳመጡትን መልሰው እንዲያነቡ፣ ወደፊትም ደግመው ደጋግመው ያለማቋረጥ እንዲያነቡ ተፅዕኖ ያሳድርባቸዋል፣ ባነበቡት ጽሑፍ ላይም በቡድን በመቀናጀት እንዲወያዩ ከተደረገ

የማንበብ ፍላጐታቸው እየጨመረ ይሄዳል፡፡ ንባቡም ልክ እንደ ምግብ በህይወት ዘመናቸው ሁሉ እንደሚያስፈ‚ጋቸው ከሚያመኑበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች የማንበብን ብልሃት በአግባቡ ተጠቅመው ያነበቡትን በትክክል ለመረዳት ይችሉ ዘንድ ጥሩ አንባቢያን ሊያስኝ የሚችል ተጨማሪ ባህርያትን ማየት ወይም ለጥሩ አንባቢነት የሚረዱ ጥያቄዎችን ማንሳት ተገቢ ይሆናሉ፡፡ ጥያቄዎቹም፤

- ጥሩ አንባቢያን የማንበብ ብልሃቶችን እንዴት ሊጠቀሙ ይችላሉ?
- ጥሩ አንባቢያን የሚከተሉት የማንበብ ሂደት ምን አይነት ነው?
- ጥሩ አንባቢያን በሚያነቡበት ወቅት ምን ያደርጋሉ?
- የማንበብን ዓላማ ከመረዳት አንፃር ጥሩ አንባቢያን ጥሩ የማንበብ ሂደትን ይከተላሉ?

የሚሉት ሲሆኑ በተለይም አካላዊ፣ አእምሯዊና ስነ-ልቦናዊ ተግባር የሚከናወነበት ንባብ ውስብስብ ሂደት አጠቃላይ ግቡ ለማንበብ መማርን ወደ ለመማር ማንበብ ማሳደግ ነው፡፡ ብሎ ብራውን (2006፡130) ሰዊት እና ሳናው ጠቅሶ ገልፆል፡፡ እንደ ብራውን (2006፡113) ገለፃ ደግሞ የማንበብ ብልሃት አምስት ጠቀሚ ቁምነገሮች መያዝ እንዳለበት በመጠቆም እነሱም አምስት የማንበብ ብልሃት ጠቃሚ ደብልዩዎች ($5W_5$) በማለት ይመድቧቸዋል፡፡ ለማንበብ ብልሃት አጋዦች አምስቱ ጠቃሚ ደብልዩዎች ($5W_5$)




Fan.(2003:223),Learning Strategy

ከላይ የቀረበው ቻርት የሚያመለክትው ጥሩ አንባቢያን ከዐውዱ ጋር ጥሩ መስተጋብር ፈጥረው በሚያነቡበት ወቅት ከላይ የተጠቀሱትን ዋና ዋና የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን ተገንዝበው የሚያነቡትን መረዳት ከቻሉ አንብቦ የመረዳትና የመገንዘብ ችሎታው እየዳበረ ከመሄዱም ባሻገር የማንበብ ፍላጎታቸው ይጨምራል (ብራውን 2006)

## 2.5. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃዎች

የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለመለካት የተለያዩ ፈተናዎች ሊሰጡ ይችላሉ። ነገር ግን አንድ ተፈታኝ በቂ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አለው ወይም የአንብቦ መረዳት ችሎታቸው ከሚጠበቃው በታች ነው ለማለት የሚቻለው የተፈታኙ ውጤት ከምን ደረጃ ደርሶ ሲገኝ ነው ለሚለው ጥያቄ ሁይጅ (1995፣119) እና ናታል (1987:35) ሲገልጹ ተፈታኙ ከ10 ከታረመ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና 9 እና 10 ያገኘ ተፈታኝ ከፍተኛ ችሎታ ያለው፣ ከ7 እስከ 8 ያገኘ ተፈታኝ በቂ ችሎታ ያለው ሲሆን በአንጻሩ ከ5 እስከ 6 ውጤት ያገኘ ተፈታኝ ዝቅተኛ እና ከ5 በታች ያስመዘገበ ተፈታኝ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ የአናብቦ መረዳት ችሎታ ያለው ተደርጎ ተወስዷል። ይህ አከፋፈል ከላይ በተለያዩ ምሁራን የቀረቡ ሀሳቦችን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ተማሪዎች በሚሰጣቸው የአንብቦ መረዳት ፈተና ከሚያገኙት ውጤት በመነሳት የሚያገኙትን ደረጃ ለማቅረብ አስችሏል።

# ምዕራፍ ሶስት፤ የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የተማሪዎች ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በአይነቱ መጠናዊ በመሆኑ ተዛምዷዊ የምርምር ስልትን ተከትሎ ተከናውኗል፡፡ የተማሪዎች ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ግንዛቤ በፅሁፍ መጠይቅ፣ የአንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ደግሞ በፈተና ተለክቷል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎችም መጠናዊ በሆነ መንገድ ተተንትነዋል፡፡

## 3.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በአመቺ ናሙና በተመረጠው በምዕራብ ሸዋ ዞን በኢሉ-ገለን ወረዳ በኢጃጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን የዚህ ምክንያት ትምህርት ቤቱ በከተማው የሚገኝ ብቸኛ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መሆኑና በተጨማሪም አጥኝዋም የምታስተምርበት ትምህርት ቤት በመሆኑ ትክክለኛና ተገቢውን መረጃ በቅርበት ለመሰብሰብ ያመቻል ተብሎ ስለታመነበት ነው፡፡

የጥናቱ ተሳታፊዎች በ2013 ዓ.ም የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በትምህርት ቤቱ ከሚማሩት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ለጥናቱ በዓላማ ተኮር ስልት እንዲመረጡ ተደርጓል፡፡ የተመረጡበትም ምክንያት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የመጀመሪያው እርከን መሆኑና በተጨማሪም በእድሜያቸውና በትምህርት ደረጃቸው ከታችኞቹ የክፍል ደረጃዎች ከፍ ያሉ በመሆናቸው፣ አጥኝዋ በዚህ የክፍል ደራጃ በማስተማር ላይ መሆኗና ስለማህበረ ስሜታዊነት የተሻለ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ስለታመነበት ነው፡፡ በተጨማሪም ከጥናቱ አንፃር የጥናቱ አካለይ አባላት በቂ መረጃ ሊሰጡ ይችላሉ ተብሎ ስለታመነበት ነው፡፡ የወካይ ናሙና ቁጥር አነስተኛ የሚሆንበት ምክንያት በቂ ገንዘብ እና አመቺ ጊዜ ሳይኖር ሰፊ ከሆነ አካላይ በርካታ ቁጥር ያለው ናሙና ወስዶ ከማጥናት ይልቅ አነስተኛ ቁጥር ያለው ናሙና መርጦ ማጥናት የተሻለ መሆኑን በመገንዘብ ነው፡፡ ያለው (2006)፡፡

በትምህርት ቤቱ በቅድመ ጥናት በተገኘ መረጃ በ2013 ዓ.ም ትምህርታቸውን የሚከታተሉ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛታቸው 330 ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከሚማሩት የዘጠነኛ ክፍል

ተማሪዎች 30% ያህሉን ከእድል ሰጭ የንሞና ዘዴ ውስጥ ረድፋዊ የንሞና ዘዴን በመጠቀም 100 ተማሪዎች እንዲሳተፉ ተደረጓል፡፡ አመራረጡም በሁሉም የመማሪያ ክፍል የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ስምዝርዝር በሰንጠረዥ በማስፍር ከስም ዝርዝሩ ከ1-10 ከሚገኙ ተማሪዎች መካከል አንዱን በእጣ በመምርጥና ከተመረጠው እጣ በመጀመር በየአስር ተማሪ ርቀት የሚገኙ ተማሪዎችን እየመረጡ በመውሰድ ነው፡፡ ሂደቱም 100 ተሳታፊ ተማሪዎች እስኪመረጡ ድረስ ቀጥሏል፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን አላማ መሰረት በማድረግ ለዚህ ጥናት የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጽሁፍ መጠይቅና የአንብቦ መረዳት ፈተና ናቸው፡፡

### 3.3.1 የጽሁፍ መጠይቅ

የመጠይቁ ዋና አላማ የተማሪዎችን ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃትና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ ምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ በመሆኑም መጠይቁ የተማሪዎች ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት አጠቃቀም ምን እንደሚመስል ለመፍተሽ መረጃ ለመሰብሰብ ውሏል፡፡ በመሆኑም መጠይቁ (ራስን የማበረታታት ብልሃት፣ ጭንቀትን የመቀነስ ብልሃት፣ የመጠየቅ ብልሃትና በትብብር የመስራት ብልሃትን) የሚመለከቱ 16 ዝግ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ኦክስፎርድ (1989) ካሰፈሯቸው ዝርዝር የቋንቋ ብልሃቶች (Strategy of Inventory for language Learners (SILL) በመተርጎም የተማሪዎች ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት የሚያሳይ ሆኖ እንዲዘጋጁ ተደርጓል፡፡ መጠይቁ ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ መወሰኛ ባለአምስት ነጥብ ምርጫ የሊክርት ስኬል መመዘኛ ልኬትን ተከትሏል፡፡ እነሱም ከከፍተኛ ወደዝቅተኛ፡ በጣም እሰማማለሁ (5)፣ እሰማማለሁ (4)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ (3)፣ አልሰማማም (2) እና በጣም አልሰማማም (1) የሚሉ ናቸው (የመጠይቁ የአማርኛ ቅጅ በአባሪ ሀ1 ላይ፤ የእንግሊዝኛው ቅጅ ደግሞ በአባሪ ሀ2 ላይ ተመልክቷል)፡፡

ጥያቄዎቹ ወደአማርኛ ተተርጉመው ማሻሻያ ተደርጎባቸው በጥናቱ አማካሪ እና በአጥኟዋ የማስተካከያ ሀሳብ ተጨምሮ ሥራ ላይ ውለዋል፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ ለዋናው መረጃ መሰብሰቢያነት ከማገልገሉ አስቀድሞ በሙከራ ጥናቱ ወቅት (pilot study) በዋናው ጥናት ያልተሳተፉ 30 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲሞሉት ተደርጎ አስተማማኝነቱ በክሮምባህ

ተፈትሿል፤ ውጤቱም የመጠይቁን አስተማማኝነት የሚያረጋግጥ ሆኖ በመገኘቱ (α = .805) የዋናው ጥናት መረጃዎች ተሰብበውበታል (የመጠይቁ አስተማማኝነት የተፈተሸበትን በሙከራው ጥናት ወቅት የተሰበሰበ መረጃ ውጤት በአባሪ ለ1 ላይ ይመለከቷል) ።

## 3.3.2 አንብቦ የመረዳት ፈተና

በጥናቱ የአንብቦ የመረዳት ፈተና የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሏል። የፈተና ጥያቄዎቹም የምንባቡን ጥልቅ መልክት አንብቦ መረዳትን፣ ከጽሁፉ የቀረቡ ዝርዝር መረጃዎችን መለየትና አንድምታዊ ሃሳቦችን የመረዳት ችሎታ የሚለኩ ሆነው ተዘጋጅተዋል።

አንብቦ የመረዳት ፈተናው በአጥኝዋ በተመረጡ ሁለት ምንባቦች ላይ የተመሰረቱ 20 ጥያቄዎች ተዘጋጅቷል። በመጀመሪው ምንባብ አንድ ከተካቱ 10 ጥያቄዎች መካከል 5 ምርጫ እና 5 አጭር መልስ ስጥ የሚሉ ጥያቄዎች አሉ። በሁለተኛው ምንባብ ከሚገኙት 10 ጥያቄዎች መካከል 5ቱ ምርጫ ሲሆኑ 5ቱ ደግሞ እውነት ወይም ሀሰት በማለት የሚመለሱ ናቸው። ፈተናው ጥናቱ በተካሄደበት ትምህርት ቤት ረጅም እድሜ በማስተማርና በመፈተን ልምድ ባላቸው መምህራን ተፈትሾ በተሰጡት አስተያየቶች መሰረትም ተስተካክሏል።

ፈተናው በዚህ መንገድ ከተዘጋጀ በኋላ ለዋናው ጥናት ከመዋሉ አስቀድሞ አስተማማኝነቱን ለማረጋገጥ በዋናው ጥናት በማይሳተፉ 30 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጎ በአንድ አራሚ (በአጥኚዋ) ታርሞ ውጤቱ ተመዝግቧል። ፈተናው በአንድ አራሚ ብቻ የታረመበት ምክንያትም ጥያቄዎቹ ቁርጠኛ መልስ (objective answer) ያላቸው በመሆናቸው ነው። የፈተናው እያንዳንዱ ጥያቄ 1 ነጥብ እንዲይዝ የተደረገ ሲሆን፤ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች በትክክል ለመለሷቸው ጥያዎች 1 ነጥብ፣ በትክክል ላልመለሷቸው ጥያቄዎች ደግሞ 0 እንዲመዘገብላቸው ተደርጎ አስተማማኝነቱ በኩደር-ሪቻርድሰን 20 ($KR_{20}$) ተሰልቷል። በዚህም መሰረት የፈተናው አስተማማኝነት ጥሩ እንደሆነ ከውጤቱ ($KR_{20}$ = .710) መረዳት በመቻሉ የዋናው ጥናት መረጃዎች ተሰብስበውበታል (በሙከራው ጥናት ወቅት የተሰበሰበው የፈተናው አስተማማኝነት የተፈተሸበት የአንብቦ መረዳት ፈተናው ውጤት በአባሪ ለ2 ላይ ተመልክቷል)።

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

የጥናቱን ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ሲባል መረጃዎች በጽሁፍ መጠይቅና በአንብቦ መረዳት ፈተና ተሰብስበው በSPSS version 23 አማካይነት፤ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ እና በህብረ ድህረት ተተንትነዋል:: ከትንተናው በፊትም መረጃዎቹ፣ (ሀ) የስርጭት ወጥነት መኖር፣ (ለ) ቀጥተኛ ተዛምዶ መኖር፣ (ሐ) በነጻ ተላውጦዎች መካከል ፈርጀ ብዙ ተዛምዶ (multicollinearity) አለመኖር እና (መ) Homoscedasticity (በነጻ ተላውጦዎቹ ባለው እያንዳንዱ ዋጋ ትይዩ በጥገኛው ተላውጦ የሚገኙ ዋጋዎች መደበኛ ልይይት ተመሳሳይነት) የተሰኙትን የፒርሰን ተዛምዶ መወሰኛ እና የህብረ ድህረት መሰረታዊ እሙኖችን (assumptions) ማሟላታቸው ተፈትሿል::

በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት፤ ማለትም፣ የአጠቃላዩ ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት እና የማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ክፍሎች የሆኑት ራስን ማበረታታት፣ ጭንቀትን መቀነስ፣ በትብብር መስራትና መጠየቅ መረጃዎች፤ እንዲሁም በፈተና የተገኙት የአንብቦ መረዳት መረጃዎች የስርጭት ወጥነትን (normal distribution) የሚያሟሉ መሆናቸው በግድለት (Skewness) ዜድ ውጤት እና በዝብጠት (Kurtosis) ዜድ ውጤት ተፈትሿል:: በፍተሻው የተገኙት የዜድ ውጤት ስሌቶችም በ-1.96 እና በ1.96 መካከል የሚገኙ በመሆናቸው እሙኑ እንደሚሟላ ለማረጋገጥ ተችሏል (የዜድ ውጤት ስሌቶቹ በአባሪ ሐ1 ላይ ተመልክተዋል)::

ተንባይ ተላውጦዎቹ፤ ማለትም አጠቃላዩ ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት እና የማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ክፍሎች የሆኑት ራስን ማበረታታት፣ ጭንቀትን መቀነስ፣ በትብብር መስራትና መጠየቅ ከተተንባይ ተላውጠው (አንብቦ መረዳት) ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ (Linear Relationship) ያላቸው መሆኑ በብትን ግራፍ (Scatterplot) ተፈትሾ እያንዳንዱ ብትን ግራፍ ከሞላጎደል ሞለል ያለ ቅርጽ (oval shape) አሳይቷል፤ ከዚህም የቀጥተኛ ተዛምዶ እሙን መሟላቱን ለመረዳት ተችሏል (ብትን ግራፉን በአባሪ ሐ2 ላይ ይመለከቷል):: በነጻ ተላውጦዎች መካከል ፈርጀብዙ ተዛምዶ (multicollinearity) አለመኖሩ በTolerance እና በVariance Inflation Factor (VIF) የተፈተሸ ሲሆን ውጤቱም እሙኑ መሟላቱን አረጋግጧል (መረጃውን በአባሪ ሐ3 ይመለከቷል)::

Homoscedasticity (በነጻ ተላውጦዎቹ ባለው እያንዳንዱ ዋጋ ትይዩ በጥገኛው ተላውጦ የሚገኙ ዋጋዎች መደበኛ ልይይት ተመሳሳይነት) በz Predicted እና በz residual መካከል

ባለ ግንኙነት በብትን ግራፍ አማካኝነት ተፈትሾ ከተገኘው ውጤት እሙኑ እንደተሟላ ለማወቅ ተችሏል (መረጃውን በአባሪ ሐ4 ይመለከቷል) ፡፡

እሙኖቹ መሟላታቸው በዚህ መንገድ ከተረጋገጠ በኋላ መረጃዎቹ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ እና በህብረ ድህረት ተተንትነው የምርምሩ ጥያቄዎች ተመልሰዋል (የዋናው ጥናት በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ በአባሪ መ1 ላይ፤ የዋናው ጥናት በፈተና የተሰበሰበው መረጃ ደግሞ በአባሪ መ2 ላይ ተመልክተዋል) ፡፡

# ምዕራፍ አራት፤ የውጤቱ ትንተና እና ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ጥያቄዎች ሁለት ናቸው። ጥያቄዎቹን ለመመለስ በጽሁፍ መጠይቅና በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነዋል። የጥናቱ የመጀመሪያ ጥያቄ “ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ከተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል?” የሚል ነው። ጥያቄውን ለመመለስ በጽሁፍ መጠይቅና በአንብቦ መረዳት ፈተና ከ100 የጥናቱ ተሳታፊ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተገኙት መረጃዎች በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተተንትነዋል። የትንተናው ውጤትም በሰንጠረዥ 4.1 ቀርቧል።

በሰንጠረዥ 4.1፤ የማህበረ ስሜታዊ ብልሃትና የአንብቦ መረዳት ተዛምዶ፣ በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ

| ተላውጦዎች | አንብቦ መረዳት | ጉልህነት (በባለሁለት ጫፍ) |
|---|---|---|
| 1. በአጠቃላይ ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት | .633 | <.001 |
| 2. ራስን የማበረታታት ብልሃት | .423 | <.001 |
| 3. ጭንቀትን የመቀነስ ብልሃት | .518 | <.001 |
| 4. በትብብር የመስራት ብልሃት | .576 | <.001 |
| 5. የመጠየቅ ብልሃት | .699 | <.001 |

በሰንጠረዥ 4.1 እንደተመለከተው በአጠቃላዩ ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት እና በአንብቦ መረዳት ውጤት መካከል ጉልህ አወንታዊ ተዛምዶ (r= .633፣ P<.001) አለ። ይህ ተዛምዶም ጠንካራ ሲሆን (ፓለንት፣ 2010፣ 134)፤ ሁለቱ ተላውጦዎች የተጋሩት ባህሪም 40.07% ነው። ከዚህም በሁለቱ ተላውጦዎች (በአጠቃላይ ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት እና በአንብቦ መረዳት) መካከል የታየው ጉልህ ስታትስቲክሳዊ የተዛምዶ አቅጣጫ የአንደኛው መጨመር ወይም መቀነስ በሌላኛው መጨመር ወይም መቀነስ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ራስን የማበረታታት ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር ያለው ተዛምዶም እንዲሁ በስታትስቲክስ

ጉልህ አወንታዊ (r=.423፣ P<.001) ሲሆን የተዛምዶው ጥንካሬም መካከለኛ ሆኗል፡፡ ሁለቱ ተላውጦዎች የሚጋሩት ባህሪም 17.90% እንደሆነ ውጤቱ አሳይቷል፡፡

እንዲሁም ጭንቀትን በመቀነስ ብልሃትና በአንብቦ መረዳት ውጤት መካከል ያለው ተዛምዶ በስታትስቲክስ ጉልህ አወንታዊ (r= .518፣ P<.001) መሆኑን ከሰንጠረዥ 4.1 መረዳት ይቻላል፡፡ በእነዚህ ሁለት ተላውጦዎች መካከል ያለው ተዛምዶ ጥንካሬም ከፍተኛ ነው (ፓለንት፣ 2010፣ 134) ፡፡ ተላውጦዎቹ የሚጋሩት ባህሪም 26.83% ነው፡፡ በአንብቦ መረዳት ውጤትና በትብብር የመስራት ብልሃት መካከል ያለው ተዛምዶም እንደቀደሙት ሁሉ በስታትስቲክስ ጉልህ አወንታዊ (r= .576፣ P<.001) ሆኗል፡፡ እነዚህ ሁለት ተላውጦዎች 33.18% ባህሪ የሚጋሩ ሲሆን፣ በፓለንት (2010፣ 134) መሰረት በመካከላቸው ያለው ተዛምዶ ጥንካሬም ከፍተኛ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

በሰንጠረዥ 4.1 እንደተመለከተው በመጨረሻው ብልሃት (የመጠየቅ ብልሃት) እና በአንብቦ መረዳት ውጤት መካከል ያለው ተዛምዶም እንደሌሎቹ ሁሉ በስታትስቲክስ ጉልህ አወንታዊ (r= .699፣ P<.001) ሲሆን፣ ጥንካሬውም ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሁለቱ ተላውጦዎች (የመጠየቅ ብልሃና አንብቦ የመረዳት ውጤት) የሚጋሩት ባህሪም 48.86% እንደሆነ ታውቋል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በቀረበው የውጤት ትንተና መሰረት፣ በማህበረ ስሜታዊ ብልሃቶች እና በአንብቦ መረዳት ውጤት መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ አወንታዊ ተዛምዶ እንዳለ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የተዛመዷቸው ጥንካሬም ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እንደሆነ ታውቋል፡፡ በማህበረ ስሜታዊ ብልሃቶቹ አንድ ባንድ ከአንብቦ መረዳት ውጤት ጋር የሚጋሩት የባህሪ መጠንም በመቶኛ ተሰልቶ ታውቋል፡፡

የጥናቱ ሁለተኛው ጥያቄ “ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳች ችሎታ ለመተንበይ ያለው ድርሻ ምን ያህል ነው?” የሚል ነው፡፡ በዚህም መሰረት የማህበረ ስሜታዊ ብልሃቶቹ በጥምርና በተናጠል የአንብቦ መረዳት ውጤትን በመተንበይ ረገድ ያላቸውን ድርሻ ለማወቅ ሲባል በሰንጠረዥ 4.2 እንደተመለከተው መረጃዎቹ በህብረ ድህረት ትንተና ተፈትሸዋል፡፡

ሰንጠረዥ 4.2፤ የማህበረ ስሜታዊ ብልሃት የአንብቦ መረዳት ውጤትን የመተንበይ ድርሻ፣ በህብረ ድኅረት

| ተንባይ ተላውጦዎች | ህብረ ተዛምዶ | የተጋርቶ መጠን ($R^2$) | የF ዋጋ | የነጻነት ደረጃ (df) | የP ዋጋ | ድህረታዊ መጣኝ (B) | መደበኛ ድህረታዊ መጣኝ (β) | የt ዋጋ | የP ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ሞዴል (የማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ክፍሎች በጥምረት) | .754 | .569 | 31.34 | (4፣ 95) | <.001 | | | | |
| ራስን የማበረታታት ብልሃት | | | | | | -0.287 | -0.350 | -3.19 | .002 |
| ጭንቀትን የመቀነስ ብልሃት | | | | | | 0.025 | 0.026 | 0.2 5 | .802 |
| በትብብር የመስራት ብልሃት | | | | | | 0.340 | 0.308 | 3.33 | .001 |
| የመጠየቅ ብልሃት | | | | | | 0.685 | 0.752 | 6.55 | <.001 |

* ተተንባይ ተላውጦ፤ አንብቦ የመረዳት ችሎታ

በሰንጠረዥ 4.2 እንደተመለከተው ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት (የማህበረ ስሜታዊ ብልሃቶች በአንድነት ሆነው) አንብቦ የመረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻቸው፤ $R^2$ = .569፣ F(4, 95) = 31.34, P = <.001 ነው፤ ይህም አራቱ ተንባይ ተላውጦዎች በጥምር ሆነው አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመተንበይ ያላቸው ድርሻ በስታትስቲክስ ጉልህ መሆኑን ያሳያል:: የትንበያ ውጤቱም፣ በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ልዩነት 56.9% ($R^2$ = .569) ያህሉ በማህበረ ስሜታዊ ብልሃቶች በጥምር ሊገለጽ እንደሚችል የሚያሳይ አንድምታ ያለው ነው::

ራስን የማበረታታት ብልሃት በተናጥል አንብቦ የመረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው (β = -0.350፣ t = -3.19, P=.002) እንደሆነ በሰንጠረዥ 4.2 የቀረበው ትንተና ያሳያል:: ከዚህም

ራስን የማበረታታት ብልሃት አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመተንበይ ያለው ድርሻ በስታትስቲክስ ጉልህ አሉታዊ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡ የተጋርቶ መጠን ስሌቱም 14.81% ይሆናል፡፡ በሌላ አባባል 14.81% የሚሆነው በተማሪዎች መካከል የሚታየው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት ልዩነት ራስን ማበረታታት በተሰኘው ብልሃት እንደሚገለጽ (explain እንደሚሆን) ያሳያል፡፡

በትብብር የመስራት ብልሃት በተናጥል የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው በስታትስቲክስ ጉልህ አወንታዊ መሆኑን፣ የተገኘው ውጤት ($\beta = 0.308$፣ $t = 3.33$፣ $P = .001$) ያሳያል፡፡ የተጋርቶ መጠኑም 17.74% ነው፡፡ ከዚህም 17.74% የሚሆነው በተማሪዎች መካከል የሚታይ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት ልዩነት በትብብር መስራት በተባለው ብልሃት እንደሚገለጽ ያመለክታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የመጠየቅ ብልሃት ለብቻው የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ በስታትስቲክስ ጉልህ አወንታዊ እንደሆነ ውጤቱ ($\beta = 0.752$፣ $t = 6.55$፣ $P < .001$) አመላክቷል፡፡ የተጋርቶ መጠኑም 52.56% ይሆናል፡፡ ከዚህም 52.56% የሚሆነው በተማሪዎች መካከል የሚታይ ከተተንባይ ተላውጦ አኳያ ያለ ልዩነት በዚህ ተንባይ ተላውጦ እንደሚገለጽ መረዳት ይቻላል፡፡

ይሁንእንጂ ጭንቀትን የመቀነስ ብልሃት የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ በስታትስቲክስ ጉልህ ሆኖ አለመገኘቱን ውጤቱ ($\beta = 0.026$፣ $t = 0.25$፣ $P = .802$) አመልክቷል፡፡ በዚህ ጥናት የመረጃ ውጤት መሰረትም ተንባይ ተላውጠው በተተንባይ ተላውጠው ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ የለውም ከሚል አንድምታ ላይ መድረስ ይቻላል፡፡

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ቀዳሚ ዓላማ በማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ያለውን ተዛምዶ መመርመር ነው፡፡ በዚህም መሰረት የጥናቱ ውጤት ማህበረስሜታዊ የመማር ብልሃቶች ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር በስታስቲካዊ ትንተናው ጉልህ ዝምድና እንዳላቸው አሳይቷል፡፡ የተዛመዷቸው ጥንካሬም ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተለይም ለተዛዶውም ራስን ከማበረታታት፣ በትብብር ከመስራትና ጭንቀትን ከመቀነስ የበለጠ የመጠየቅ ብልሃት ጉልህ ድርሻ እንዳለው ውጤቱ አመላክቷል፡፡ ይህ ጥናት

ከአንደርሰን (2000)፣ ወይንሸት (2007)፣ ከቾይ (2011)እና በአከዬ (2012) የጥናት ውጤት ጋር የሚደጋገፍ ነው፡፡

ሁለተኛውን የጥናቱ ዓለማ ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃት የአንብቦ የመረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው ምን ያህል እንደሆነ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህም መሰረት ውጤቱም የማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃቶች የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻቸው ጉልህ እንደሆነ አሳይቷል፡፡ ራስን የማበረታታት፣ በትብብር የመስራትና የመጠየቅ ብልሃት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በመተንበይ ረገድ ጉልህ ድርሻ እንዳላቸው ውጤቱ አመላክቷል፡፡ ነገርግን፣ ጭንቀትን የመቀነስ ብልሃት የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ በስታትስቲክስ ጉልህ ሆኖ አለመገኘቱን ውጤቱ አመላክቷል፡፡ በተናጠል ሲታይ ደግሞ የመጠየቅ ብልሃት ከፍተኛ ቦታውን ይይዛል፡፡ ይህም የመጠየቅ ብልሃት ራስን ከማበረታታትና በትብብር ከመስራት የበለጠ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ መዳበር የጎላ አስተዋጽኦ አለው የሚል አንድምታ ይኖረዋል፡፡ ይህ ጥናት ከበአከዬ (2012) እና ከቾይ (2011) የጥናት ውጤት ጋር ተደጋጋፊ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በአጠቃላይ፣ ይህ ጥናት በማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ ጉልህ ተዛምዶ እንዳለና የመተንበይ ድርሻውም ጉልህ እንደሆነ የውጤት ትንተናው አመላክቷል፡፡ በመሆኑም መምህራን አንብቦ መረዳት ችሎታን በሚያስተምሩበት ጊዜ በማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ መኖሩን በመረዳት የተማሪዎችን ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃቶችን አጠቃቀም ግምት ውስጥ ቢያስገቡ የተሻለ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፡ ማጠቃለያ፤ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳብ

## 5.1 ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታና በማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃቶች ያለውን ተዛምዶ መመርመርና ብልሃቱ የአንብቦ የመረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻው ምን ያህል እንደሆነ ለመፈተሽ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት የጥናቱን መሰረታዊው ጥያቄዎች ለመመለስ እንዲቻል ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ውለዋል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎችም በምዕራብ ሸዋ ዞን በኢሉ-ገላን ወረዳ በኢጃጂ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ም በዘጠነኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ያሉ ተማሪዎች ናቸው፡፡ በዚህ ክፍል ደረጃ ከሚማሩ 330 ተማሪዎች መካከል በእድል ሰጭ የንሙና ዘዴ የተመረጡ 100 ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያዎቹም የፅሁፍ መጠይቅ እና የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ናቸው፡፡

በፅሁፍ መጠይቁና በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰቡት መረጃዎች ገላጭና ተንባይ ስታስቲካዊ የቅመራ ዘዴዎችን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ በውጤት ትንተናው መሰረትም የማህበረ ስሜታዊ ብልሃቶችን መማርና የአንብቦ መረዳትና ችሎታን ተዛምዶ ለማየት ተሞክሯል፡፡ በዚህም የማህበረ ስሜታዊ መማር ብልሃቶች ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ጉልህ አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ ከዚህ አኳያ የተማሪዎች የአንብቦ የመረዳት ችሎታ ራስን ከማበረታታት፣ በትብብር ከመስራት፣ ጭንቀትን ከመቀነስና ከመጠየቅ ብልሃት አጠቃቀማቸው ጋር ጉልህ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡

በተጨማሪም የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው የማህበረስሜታዊ መማር ብልሃቶች በአንድነት የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻቸው ከፍተኛ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ በተናጠል ሲታይ ደግሞ የመጠየቅ ብልሃት ራስን ከማበረታታትና በትብብር ከመስራት በበለጠ የመተንበይ ድርሻ እንዳለው ከውጤቱ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን ጭንቀትን የመቀነስ ብልሃት የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ በስታትስቲክስ ጉልህ ሆኖ አለመገኘቱን ውጤቱ አመላክቷል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

የጥናቱን ውጤትና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያ ላይ ተደርሷል፡፡ አንደኛ፣ በተማሪዎች ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃቶችና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል የጎላ አወንታዊ ተዛምዶ አለ፡፡ ለተዛምዶውም ከፍተኛውን ቦታ በመያዝ ጉልህ ድርሻ ያሳየው የመጠየቅ ብልሃት ነው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎች የማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃት ግምት ውስጥ በማስገባት ማስተማር የአንብቦ መረዳት ችሎታቸውን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል የሚል አንድምታ አለው፡፡

ሁለተኛ፣ የማህበረ ስሜታዊ መማር ብልሃቶች በአንድነት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ድርሻቸው ጉልህ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡ በተናጠል ሲታይም የመጠየቅ ብልሃት ጉልህ ድርሻ እንዳለው ታይቷል፡፡ ይህም የመጠየቅ ብልሃት ራስን ከማበረታታትና በትብብር ከመስራት የበለጠ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ መዳበር የጎላ አስተዋጽኦ አለው የሚል አንድምታ ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ግን በተናጠል ሲታይ ደግሞ ጭንቀትን የመቀነስ ብልሃት የአንብቦ መረዳት ችሎታን የመተንበይ ድርሻ በስታትስቲክስ ጉልህ ሆኖ አለመገኘቱን ውጤቱ አመላክቷል፡፡

## 5.3 የመፍትሄ ሀሳብ

በዚህ ጥናት የተደረሰባቸውን ውጤቶች ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል የሚከተሉትን መፍትሄዎች ተጠቁመዋል፤

አንደኛ፣ በጥናቱ በማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃትና በአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለ አሳይቷል፡፡ በመሆኑም የአማርኛ ስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች የዘጠነኛ ክፍልን የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያና የመምህሩ መምሪያ መፅሀፍት ሲያዘጋጁ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚጠቅሙ ብልሃቶችን ከዝርዝር አተገባበራቸው እንደ አንድ ይዘት ቢያካትቱ ውጤታማ ያደርጋል፡፡

ሁለተኛ፣ ማህበረ ስሜታዊ የመማር ብልሃቶች በርካታ ቢሆኑም በዚህ ጥናት ትኩረት የተሰጣቸው ራስን የማበረታታት፣ በትብብር የመስራት፣ ጭንቀትን የመቀነስና የመጠየቅ ብልሃት ብቻ ናቸው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ጥናት ማካሄድ የሚሹ ተመራማሪዎች በእነዚህና በዚህ ጥናት ባልተዳሰሱ የማህበረ ስሜታዊ ክፍሎች (የጋራ ስሜትን መቆጣጠርና የሌሎችን ችግር መጋራት (እንደራስ ማየት) በመተጋገዝ መስራት ላይ ሰፋ ያለ ጥናት ቢያካሂዱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ቀላል አይሆንም፡፡

# ዋቢዎች


ማረው አለሙ ፡፡ (1998) ፡፡ *አማርኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ዘዴ*፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ ፡፡ (1986) ፡፡ *አንብቦ የመረዳትና የመፃፍ ችሎታን ማዳበር*፡፡አዲስ አበባ፣ ት.ማ.ማ.ድ

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡ 2004፡፡ የተማሪው አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ 9ኛ ክፍል፡፡ ኩራዝ ኢንተርናሽናል አሳታሚና የትምህርት ስራዎች አማካሪ ድርጅት፡፡ አዲስ አበባ፡፡

በላይነሽ ደነቀ ፡፡ (2002) ፡፡ በኦሮሚያ ክልል በኢሉ ባቦር ዞን በመቱ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኣፋቸውን በኦሮሚኛ የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቃላትን ለመማር የሚገለገሉባቸው የመማር ብልሃቶች ፍቴሻ ፡፡ አ.አ.ዩኒርሲቲ ለአማርኛ የ2ኛ ዲግር ማሚያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)

እንድሪስ አባይ፡፡ (2000) ፡፡ የአንብቦ መረዳት ብልሃቶችን መማር ከአነበቦ መረዳት ችሎታ ጋር ያለው ተዛምዶ፡፡ ያልታተመ የድህረ ምረቃ ቴሲስ፤ባህርዳሪ ዩኒቨርቲ

ከበደ ሚካኤ፡፡ (1994)፡፡ ታላላቅ ሰዎች፤አዲስ አበባ፤ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ከበደ አያሉ፡፡ (1999) ፡፡ የሰዋሰው ትምህርት በክፍል ውስጥ የመማሪያ ብልሃቶች አጠቃቀምና ኢተገባበር ፍተሸ አ.አ.ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግር ማሚያ የቀረበ ጥናት

ወይንሸት ግርማ፡፡ (2007) ፡፡ ማህበር ስሜታዊ ብልሃት የአማርኛ ቋንቋ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ላይ አንብቦ የመረዳት ችሎተን እና የማንበብ ፍላጎትን በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና (በጫንጮ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳረ)

ያለው እንዳወቀ፡፡ (1998) ፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ አዲስ አበበ ንግድ ማተሚያ ድርጂት

Aliakban, M, and Hayat Zadih, A. (2008). Variation Language Learning Strategies among Iranian English students: The Effect of Gender Instructional *Journals of pedagogies* 4(3)72-87 from http://WWW.Apical.(org/ijp/)V4n3/UPLV4n3-article7:pdf.

Blanden, J.M. (2017). Social Mobility to Investigate Intergenerational Links in Home

Block, C. (1992). *Teaching the Language Arts Expanding Thinking Trough Student Centered Intuition.*

Boakye, N, Y. (2012). A Socio affective approach to improving student reading comprehension ability Athesis submitted in partial fulfillment of the requirements for the degree. University of Pretoria.

Brown, H.D. (1994). *Principle of language learning and teaching*. Englewood cliffs. Prints hall Regent

Brown, H. (2006). EdgeTm.Reading, writing and Language. National Geographic School Publishing.USA.

Burry-Stock, J. A. (1995). Assessing the use of language learning Strategies worldwide with the ESL/EFL version of the strategy inventory for Language learning (SILL). System 23(1), Ownership, an Important Marker of Wealth. 23. Doi: 0346-251X (94)00047-6

Chol, K. (2011) .A Study on the effects of Socio Affactive Strategies on Reading comprehension. In Korea Univerisity College Students. From htt://WWW.CPaaljapan. Org/resources/Proceedi Ngs/PaaL7/ Pdfs/05KYUnghee.Pdf.

Cral T. (1994), Teachers' Developmenting the Right Moves U.S.A information Agency.

Dick and Catbilen. (1991). *Essential Teaching Strategies. Teaching every Child to Read*. University of Michinan.

Ellis, R. (1994). The study of secondary language acquisition. Oxford: Oxford University Press Exercises. Cambridge. Cambridge university press.

Feldman, A. (2000) (Ed). Cooperative learning the social and intellectual outcomes of learning in Groups New York: Rutledge.

Goodman .K.S (1994), Learning about psycholinguistic processes by analyzing oral reading. Harvard education Review

Grable, W& Stroller, F. (2002). Teaching and researching reading. London: Person Education.

Grellet, F. (1981).Developing Reading skills: pratical Guide to Readings Comprehension

Gunnining, T.G. (1996).Creating Reading Ins traction for All children All you and Bacon.

Habte Gabr, (2006) The Importance of Socio Affactive Strategies in Using EFL. For Teaching Mainstream Subjects. The Journal of Humanizing Language teaching .8(5).Retrrieved 15 March 2018.

Hismanoglu, M. (2000).Language learning strategies in Foreign Language Learnig and Teaching. The internet TESL journal, 6(8), forum http//iteesij.Org/Articles/.Hismanoglu. Strategies html.

Hughes, A. (1995).Testing for Language Teachers. Combridge: Combrige University Press in Groups New York: Rutledge. University of Michinan.

Johnson R. and Monsoon V. (2012). Cooperation Competition and ConstructiveControversy in Developing Professional ethics in Law School Classes. The University of St. *Thomas Law School Journal University of St. Thomas School of Law.*

Johnson, R and Monsoon, V. (2009). An Overview of Cooperative Learning from "http://www.cooperation.org/page/overviewpaper.htmal"

Knight, P. G., & Bohlmeyer, M. E. (1990). Cooperative Learning and Achievement: Methods for Assessing Causal Mechanisms. In S. Sharan (Ed.), *Cooperative Learning: Theory and Practice* (pp. 1-22). New York: Greenwood Press, Inc.

Oxford, R. (1994). Language Learning Strategies an update.
"http://www.cal.Org/resources/digest/oxfordo/.htm"

Oxford, R. (1989).Use of Language Learning stratetie s: a synthesis of studies with implications for strategy training. *System, (17)2*,235-247.

Oxford, R. L (1990). Language Learning Strategies.What every teacher showed knows. Newyor House Publishes.

O.Mally. C and Chamot, A.U. (1990).*Learning Strategies in Second Language Acquisition.* Cambridge University Press.

Pallant, J. (2011). *SPSS survival manual: A step by step guide to data analysis using SPSS.* Australia: Allen & Unwin.

Park, G.-P. (1997).Language learning strategies and English proficiency in Korean university Students. *Foreign Language Annals,* 30, 211-221.

Richard, J. C. and Renadya, W. A (2002) *.Methodology in Language teaching; an anthology of current practice.* New York: Cambridge University press.

Richards, J. C. (1985). *The context of language teaching*. Cambridge, UK: Cambridge University Press.

Richards, J. C. (1985). The *context of language teaching*. Cambridge, UK: Cambridge University Press.

Rodgers, Theodore, (2003), *Approaches and methods in language teaching*. Cambridge, Cambridge University press.

Rita Rani-mandal. (2009). Cooperative Learning Strategies to enhance writting skill, the modern

Journal of applied linguistic Volume 1:2 "http://www.coop"

Rubin, J. (1987). Learner Strategies: Theoretical Assumption, Research History and Typology. In A. Wenden and J. Rubin (eds) *Learner Strategies in Language Learning*. Englewood Cliffs, NJ. Prentice Hall.

Rut man .G. (1994). Attitude Interested in Education. Alfred Publishing.

Nuttall, C. (1987).*Teaching Reading skills for in a foreign Lnguage*.London: Heinemann Educational Books

Nattal, C. (1996). *Teaching Reading skills for in a foreign Language*. London: Macmillan Publishers Limits.

Sak, G.and James, W.W. (1997).Principles of Educational Psychological Measurement and Educational an International Thomson Publishing Company.

Sheng.He.Ji. (2000).*A cognitive model for teaching Reading compression*. Forum, 38(4), PP.12-15.

Singh, N.N. (2004). Evaluations Issues in Evidence — Based Practice. Chapter 4(71-87). *In Handbook of Interventions that work with Children and Adolescents: Prevention and Treatment.* John Wiley & Sons, Incorporated.

Smith, F (1985) Reading. Combridge: Combridge Press

Snaw, C. (2002).Reading for Understanding forward an R and D program in Reading Comprehension.Santa Monica, CA: Rand Corporation.

Stern, H .W. (1983). *Fundamental concepts in language teaching* Oxford: Oxford University Press.

Slavin R.E. (1999).Improving Intergroup Relations.Lesson learned from cooperative learning programs. Center for Research on the education of students placed at risk Johns. Hophims University. *The Journal of social issues.*

Tabanlioglu, Selim. (2003). The Relationship between Learning Style and language Learning strategies of per intermediate EAP student. MSC thesis from htt://www.Sevalfer.Com//files/DTez-Monurcesur,pdf.

Tonjis, M.J. (1991). *Secondary reading, writing, and learning*. Boston.MA: Allyn & Bacon.

Vijaya, R. J. (2012). Socio affective Strategies in Reading. 6(1), 76-100. Retrieved from "https://media.neliti.com/media/publications/222305-students-socioaffective-strategy-in-read.pdf"

Wiener, H.S. and Bazerman, C. (1997). Reading skills Hand Book.(7thed). Boston and New York Houghton Mifflin Company.

Wigfield, A. & Guthrie, J. T. (1997).Relations of children's motivation for reading to the amount and breadth of their reading. *Journal of Educational Psychology.*

Willkins, L (1982). *Instructional Techniques and Practice*. Stonly Thorontonco.

Williams, M, and Burden, R. (1997). *Psychology for language Teachers: A Social Constructivist Approach* Cambridge: Cambridge University Press.

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ፤ የማህበረ ስሜታዊነት የመማር ብልሃት የፅሁፍ መጠይቅ በአማርኛ እና በዝንግሊዝኛ ቋንቋዎች

## አባሪ ሀ1፤ የማህበረ ስሜታዊነት የመማር ብልሃት የፅሁፍ መጠይቅ በአማርኛ ቋንቋ

**ባህርዳር ዩኒቨርስቲ**

**ሂውማኒቲስ ፋኩሊቲ**

**አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል**

**ድህርምረቃ መርሀግብር**

በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

**ውድ ተማሪዎች፤** የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ **የማህበረ ስሜታዊነት የመማር ብልሃት አጠቃቀምና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ተዛምዶ** ለመመርመር ታስቦ ለሚሰራው ጥናት መረጃ ማስገኘት ነው፡፡ በመሆኑም በመጠይቁ ለተካተቱት ጥያቄዎች የሚሰጡት እውነተኛ ምላሾች ለጥናቱ ከግብ መድረስ ወሳኝ በመሆናቸው መጠይቁን በትክክል በመሙላት እንድትተባበሩኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

***<u>መመሪያ</u>፤***

የመጠይቁ አሞላል ከጥያቄዎቹ ፊት ለፊት ከ1 እስከ 5 ካሉት ቁጥሮች አንዱን ብቻ መርጦ በመክበብ ነው፡፡

በመጠይቁ በጥያቄዎቹ ፊት ለፊት ከ1 እስከ 5 ያሉት ቁጥሮች ቀጥሎ ያሉትን የውሳኔ ሃሳቦች የያዙ ናቸው፡፡

*5 = በጣም እስማማለሁ*
*4 = እስማማለሁ*
*3 = በመጠኑ እስማማለሁ*
*2 = አልስማማም*
*1 = በጣም አልስማማም*

*መጠይቁን ለመሙላት ቀጥሎ ባሉት ባዶ ቦታዎች መለያ ቁጥር፣ ክፍልና መማሪያ ክፍል፣ መጻፍና ጾታን በሚመለከት በተገቢው ቦታ ላይ ጭረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡*

መለያ ቁጥር _______የክፍል ደረጃ ______መማሪያ ክፍል ____ ጾታ፤ወንድ _____ ሴት

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች<br>በአማርኛ አንብቦ መረዳት፤ | አማራጮች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | **ራስን የማበረታታት ብልሃት** (Encouraging yourself) | | | | | |
| 1 | በሁለተኛ ቋንቋዬ አንድን ተግባር እንዳጠናቀቅኩ እራሴን አደንቃለሁ:: | | | | | |
| 2 | ሁለተኛ ቋንቋዬን ስማር በራሴ የመተማመን ስሜቴን ከፍ አደርጋለሁ:: | | | | | |
| 3 | ሁለተኛ ቋንቋዬን ስናገር ስህተቶችን እንዳልሰራ ፍርሀት ቢሰማኝም ራሴን ለማበረታታት እሞክራለሁ:: | | | | | |
| 4 | በሁለተኛ ቋንቋዬ ስማር ችግር ቢገጥመኝም ራሴን ለማበረታታት እሞክራለሁ:: | | | | | |
| | **ጭንቀትን የመቀነስ ብልሃት** (Lowering anxiety ) | | | | | |
| 5 | ሁለተኛ ቋንቋዬን ስማር ጭንቀቴን የሚያባብሱ መሰናክሎች ላይ ትኩረት አደርጋለሁ:: | | | | | |
| 6 | የቋንቋ መማር ስሜቶቼን በቀን ተቀን የግል ማስታወሻዬ እመዘግባለሁ:: | | | | | |
| 7 | ሁለተኛ ቋንቋዬን ስጠቀም ፍራቻ እንዳይገጥመኝ ዘና ለማለት ጥረት አደርጋለሁ:: | | | | | |
| 8 | ሁለተኛ ቋንቋዬን ሳጠና ወይም ስጠቀም የስሜት መረበሽ እንዳይገጥመኝ ጥረት አደርጋለሁ:: | | | | | |
| | **በትብብር የመስራት ብልሀት** (cooperating with others) | | | | | |
| 9 | በሁለተኛ ቋንቋዬ ስማር የሚኖረኝን ስሜት ለሰዎች እናገራለሁ:: | | | | | |
| 10 | ሁለተኛ ቋንቋዬን ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ልምምድ አደርጋለሁ:: | | | | | |
| 11 | የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ባህል ለመማር እሞክራለሁ:: | | | | | |
| 12 | በሁለተኛ ቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ መደበኛ የቋንቋ አጋር ወይም ጓደኛ አለኝ:: | | | | | |
| | **ጥያቄ የመጠየቅ ብልሃት** (Asking question) | | | | | |
| 13 | በሁለተኛ ቋንቋዬ ያልተረዳሁት ነገር ሲኖር ለሌላ ሰው ረጋ ብሎ እንዲናገረው ወይም እንዲደግመው እጠይቃለሁ:: | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ስናገር ማስተካከያ እንዲሰጡኝ የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን እጠይቃለሁ። | | | | | |
| 15 | የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን እገዛ እጠይቃለሁ። | | | | | |
| 16 | በሁለተኛ ቋንቋዬ ማብራሪያ ለማግኘት ጥያቄ እጠይቃለሁ። | | | | | |

ምንጭ፤ ኦክስፎርድ (1989)

**አባሪ ሀ2፤ የማህበረ ስሜታዊነት የመማር ብልሃት የፅሁፍ መጠይቅ በእንግሊዝኛ ቋንቋ**

**ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ**

**ሂውማኒቲስ ፋኩሊቲ**

**አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል**

**ድህርምረቃ መርሀግብር**
(**SocioAffective Learning Strategy**)

Dear students. I am conducting a research on the correlation between students socio-affective strategy.Your cooperation is found very important and divisive for the researches to attaints objective. Please answer the following questions by circling the response that best describes how you are. If you strongly disagree circle one, if you circle two, if you are somewhat agree circle three ,if you are agree circle four, if you are circle five. There are no rights or wrong answers. Work quickly and don't think to long about your answers. All 30 items are answered on 5 point linker scale with the following scale points.

1-Strongly Disagree
2- Disagree
3- Somewhat agree
4- Agree
5- Strongly Agree

Be sure that your responses will be secret

Thank you in advance.

| **No** | **Questions** | **Scales** | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | **1** | **2** | **3** | **4** | **5** |
| | **Encouraging yourself** | | | | | |
| 1 | I give myself tangible rewards for success. | | | | | |
| 2 | I feel confident about language learning | | | | | |
| 3 | I encourage myself to speak SL even when I am afraid of making a mistake | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | I encourage myself to take risks | | | | | |
| | **Lowering anxiety** | | | | | |
| 5 | I pay attention to physical stress barriers | | | | | |
| 6 | I write down my feelings in language diary | | | | | |
| 7 | I try to relax whenever I feel afraid of using SL. | | | | | |
| 8 | I notice if I am tense or nervous when I am studying orders using SL | | | | | |
| | **Cooperating with others** | | | | | |
| 9 | I talk to someone else about how I feel when I am learning SL. | | | | | |
| 10 | I work with other learners for practice | | | | | |
| 11 | I try to learn about the culture of SL speaker. | | | | | |
| 12 | I have a regular language learning partner | | | | | |
| | **Asking question** | | | | | |
| 13 | If I do not understand something in SL, I ask the other person to slow down or say it again. | | | | | |
| 14 | I ask SL speakers to correct me when I talk. | | | | | |
| 15 | I ask for help from SL speakers. | | | | | |
| 16 | I ask questions for clarification in SL. | | | | | |

**Sourses: Adapted from Oxford (1989) Strategy inventory for language learning (SILL).**

## አባሪለ. የአንብቦ መረዳት ፈተና

### ባህርዳር ዩኒቨርስቲ

### ሂውማኒቲስ ፋኩሊቲ

### አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል

### ድህርምረቃ መርሀግብር

ውድ ተማሪዎች፡- የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ ማህበረስሜታዊ የመማር ብልሃት ከአንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር ተዛምዶን በሚል ርዕስ ለሚካሄድ ምርምር መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መጠይቅ አማካይነት የተሰበሰበው መረጃ ለሌላ ዓላማ አይውልም፡፡ የአንተ/ቺ ትክክለኛ ምላሽ የጥናቱ ውጤት ተቀባይነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ስለሆነም የምትመልሳቸው /የምትመልሻቸው ምላሾች የራስህን/ሽን ፍላጎት በትክክል የሚያንፀባርቁ እንዲሆኑ ያስፈልጋል፡፡ ጥያቄዎችን በትዕግስት አንብበህ/ሽ በማጤን እንድትመልስ/ሽ ስጠይቅ ለምታደርግልኝ/ጊልኝ ቀና ትብብር በቅድሚያ ከልብ አመሰግናለሁ!

ማሳሰቢያ፡-

ሀ. የትኛውንም መልስ ብትሰጥ/ጪ ትክክል ወይም ስህተት አለመሆኑን ከግንዘቤ ውስጥ አስገባ/ቢ፡፡

ለ. ከሌላ ጓደኛጋር ተመካክሮ ጥያቄዎቹን መመለስ አይፈቀድም፡፡

ሐ. ለምላሽህ/ሽሽ መነሻ የምታደርገው/ጊው ከአሁን በፊት (ይህ ምርምር ከመካሄዱ በፊት) የነበረህን/ሽን ማህበረስሜታዊ የመማር ብልሃት ተግባር እንጂ ወደፊት ይኖረኛል ብለህ/ሽ የምትገምተውን /የምትገምቺውን አይደለም፡፡

መለያ ቁጥር-------------የክፍል ደረጃ------- መማሪያ ክፍል ------ጾታ፡- ወንድ -----ሴት-----

**አጠቃላይ መመሪያ፡-** ይህ ፈተና በኢጃጃ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የማህበረ ስሜታዊ ብልሃት አጠቃቀምና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶን ለመመርመር እየተካሄደ ባለው ጥናት ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተዘጋጀ ነው፡፡ ፈተናው ሁለት ምንባቦች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ምንባብ 10 ጥያቄዎች ሲኖሩት ሁሉተኛው ምንባብም በተመሳሳይ 10 ጥያቄዎችን ይዟል፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ፈተናውን ከመጀመርህ/ሽ በፊት የፈተና ገጾቹ ---መሆናቸውን አረጋግጥ/ጭ፡

***መመሪያ አንድ፡*** ከተራ ቁጥር 1-10 የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ 1-5 ላሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች ትክክለኛ መልስ የያዘ ሆሄ በመምረጥ ለእያንዳንዱ ጥያቄ በተዘጋጀው መልስ መስጫ ወረቀት ላይ ሙላ/ይ፡፡

**ምንባብ አንድ፡-እማሆይ ትሬዛ**

እማሆይ ትሬዛ እማሆይ ትሬዛ (1910-1997 እ.ኤ.አ) የሮማ ካቶሊክ መነኩሴ የነበሩ ሲሆን ድሆችንና የተገፉ ሰዎችን በመላው አለም ለመርዳት ጊዜያቸውን የሰጡ ነበሩ፡፡ በርካታ አመታትን በካልካታህንድ ውስጥ የሚሽነሪ የረድኤት ድርጅት በማቋቋም እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች በመርዳት አሳልፈዋል፡፡ በ1979 እ.ኤ.አ እማሆይ ትሬዛ የሰላምኖቤል ተሸላሚ ሆነዋል፡፡ እንዲሁም የበጎ አድራጎት አርአያ ለመሆን በቅተዋል፡፡ በ2016 እ.ኤ.አ እማሆይ ትሬዛ በሮማ ካቶሊክ ቤተክርስትያን ቅድስት ትሬዛ በመባል ከቅዱሳን ተርታ ተሰልፈዋል፡፡ እማሆይ ትሬዛ የተወለዱት በ1910 እ.ኤ.አ ከፒ የመቄዶንያ ሪፐብሊክ ውስጥ ነው፡፡ ስለልጅነት ጊዜያቸው ብዙም አይታወቅም፤ ነገርግን በወጣትነት ጊዜያቸው መነኩሴ ለመሆን እንደተጠሩ እና ድሆችን ለመርዳት ፈጣሪ እንደመረጣቸው አመኑ፡፡ በ18 አመታቸው በአየርላንድ የመነኩሴዎች ቡድን ዉስጥ ለመቀላቀል ፈቃድ አገኙ፡፡ ከጥቂት ወራት ስልጠና በኋላ ከሎሬቶ እህቶች ጋር ወደ ህንድ ለመጓዝ ፍቃድ አገኙ፡፡ መደበኛ ሀይማኖታዊ ቃለ መሃላ በ1931 እ.ኤ.አ በመፈጸ ምቅድስት የሊሴክስ ቅድስት ቴሬዛ ስያሜ ለውንስ ምመረጡ፡፡ ይህ ስም የቅዱሳን ሚሽናሪዎች ስያሜ ነው፡፡

ህንድ በደረሱበት ወቅት በመምህርነት አገልግለዋል፡፡ ሆኖምግን በካልካታ በተስፋ ፋውድህነት ምክንያት የሚሽናሪ ተራድዖ ለማቋቋም ቻሉ፡፡ የዚህሚሽንተቀዳሚ አላማ ረዳት የሌላቸው ሰዎችን መንከባከብ ሲሆን እማሆይ ትሬዛ ሌሎች ሰዎችን ማገልገል ዋነኛው የክርስቶስ ኢየሱስ አስተምሮ መርህ መሆኑ ተሰማቸው፡፡

ካልካታ ውስጥ ሁለት ጊዜ አስቸጋሪ ጊዜያትን አሳልፈዋል፡፡ የመጀመሪያው ሴኔጋል ውስጥ በ1943 እ.ኤ.አ ተከስቶ በነበረው ድርቅ ሳቢያ ሲሆን፤ ሁለተኛው በ1946 እ.ኤ.አ የተነሳው የህንዱ የእስልምና ብጥብጥ ነበር፡፡ ይህም የሆነው ህንድ ከመገንጠሏ በፊት ነው፡፡ 1948 እ.ኤ.አ በካልካታ ድሆችን ለመርዳት የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ሆኑ፡፡ መልበስ የሚወዱት የህንድ ሳሬ፣ ጠርዙ ሰማያዊ የሆነ የህንድ ቀሚስ ነው፡፡ ለበርካታ አመታት እማሆይ ትሬዛና ጥቂት የህንድና ሌሎች መነኩሴዎች በቀን ውስጥ አነስተኛ መጠን ያለው ገቢና ምግብ እያገኙ

አብዛኛውን ጊዜ ገንዘብ ለመሰብሰብ ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ነገርግን ቀስበቀስ ለድሆች ያላቸው ፍቅርና እንክብካቤ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እየተደነቀላቸውና በህንድ ፖለቲከኞችም ጭምር እየተወደሰላቸው መጣ፡፡

በ1952 እ.ኤ.አ የመጀመሪያውን ቤት ህይወታቸው ለሚያልፍ ሰዎች አዘጋጁ፡፡ ህይወታቸው ለማለፍ ጫፍ ላይ ከደረሱ ሰዎች ጋር ጊዜያቸውን ብዙ ጌዜ ማሳለፍ ይወዳሉ፡፡ ስራቸው በመላው ዓለም ተስፋፋ፡፡ በ2013 እ.ኤ.አ በ130 ሀገራት የሚሰሩ ሰባት መቶ ሚሽነሪዎች ነበሩ፡፡ የስራቸው ስፋት ወላጆች የሞቱባቸውንና የማይድን በሽታ የያዛቸውን ሰዎች ማካተት ጀመረ፡፡

እማሆይ ትሬዛ ሌሎች ሰዎች እምነታቸውን እንዲቀይሩ ለመስበክ ሞክረው አያውቁም፡፡ በእሳቸው የእንክንካቤ ድርጅት ውስጥ ማንኛውም ሰው የራሱን እምነት እንደጠበቀ ይቆያል፡፡ ሆኖም ግን እማሆይ ትሬዛ በካቶሊክ ሀይማኖት የጠበቀ እምነት አላቸው፡፡ በዚህም መሰረት ውርጃ፣ የሞት ቅጣት እንዲሁም ፍቺን በአለም ውስጥ ታዋቂ ሳይሆኑ ጀምሮ በጥብቅ ይቃወማሉ፡፡ በ1979 እ.ኤ.አ የሰላም ኖቤል ሽልማት “ድህነትንና ማጣትን ለማሸነፍ ትግል ውስጥ ባበረከቱት አስተዋጽኦ” ከውጪ ተሸልመዋል፡፡ ነገርግን እማሆይ ትሬዛ በሽልማት ስነስርዓቱ ላይ አልተገኙም፡፡ ከሽልማቱ የተበረከተላቸውን 192,000.00 ዶላር ለድሆች እንዲሰጥ ጠይቀዋል፡፡

ባለፉት ሁለት አስርት አመታት እማሆይ ትሬዛ በበርካታ የጤና ችግሮች ሲሰቃዩ ቆይተዋል፡፡ ነገርግን ይህንን ድሆችን እና ያጡ ሰዎችን የመርዳት ተልዕኳቸውን አላቋረጡም ነበር፡፡ በመጨረሻዎቹ ጥቂት አመታት ጊዜ ውስጥ ኒውዮርክ ብሮንክስ ውስጥ ከልዕልት ዲያና ጋር ተገናኙ፡፡ ሁለቱም የሞቱት በአንድ ሳምንት ጊዜ ነው፡፡ የእማሆይ ትሬዛን ሞት ተከትሎ ቫቲካን ስለእሳቸው መልካም ስራ የማስዋብ እንቅስቃሴ በመጀመር እሳቸውን ቅድስት አድርጎ ለመሰየም ሁለተኛውን እርምጃ ወስደዋል፡፡ እማሆይ ትሬዛ በጥቅምት 2003 እ.ኤ.አ በዳግማዊ ፖፕ ጆንፖል በመደበኛነት ቅድስት ሆነዋል፡፡

(ምንጭ - የዓለማችን የታላላቅ ሰዎች ታሪክ)

***መመሪያ አንድ፡-*** ከዚህ በታች የቀረቡትን አምስት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ለእያንዳንዳቸዉ ከተሰጡት ምርጫዎች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘዉን ሆሄ በመክበብ መልስ/ሽ፡፡

1. የእማሆይ ትሬዛ ተግባር ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. የሚሽነሪ ተቋም አቋቁመዋል፡፡ ሐ. በመምህርነት አገልግለዋል፡፡

ለ. በእምነታቸው ዙሪያ ስብከት አካሂደዋል፡፡ መ. የሰላም ኖቤል ተሸላሚ ሆነዋል፡፡

2. እማሆይ ትሬዛ በዓለም ታዋቂ ሳይሆኑ በጥብቅ የሚቃወሙት ጉዳይ ምን ነበር?

ሀ. ውርጃ ለ. የሞት ቅጣት ሐ. ፍቺ መ. ጋብቻ

3. እማሆይ ትሬዛ ያቋቋሙት የሚሽነሪ ተራድኦ ብዛት በ2013 እ.ኤ.አ ስንት ደርሶ ነበር

ሀ. 800 ለ. 700 ሐ. 7000 መ. 130

4. እማሆይ ትሬዛ እ.ኤ.አ መቸ ተወለዱ?

ሀ. 1990 ለ. 1910 ሐ. 1997 መ. 1990

5. እማሆይ ትሬዛ የቅድስትነት ማእረግ በማን ተሰጣቸው?

ሀ. በዳግማዊ ፖፕ ጆን ፖል ሐ. በካልካታ በሚኖሩ ሰዎች

ለ. በአየርላነድ መነኩሴዎች መ. በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን

***መመሪያ ሁለት***፡- ከዚህ በላይ የቀረበውን ምንባብ በጥንቃቄ በማንበብ ከ6-10 ለቀረቡት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጭ፡፡

6. እማሆይ ትሬዛን የሚሽነሪ ተራድኦ ለማቋቋም ያነሳሳቸው ምክንያት ምን ነበር?

7. የአንቀጽ ሁለትን ጭብጥ ሃሳብ በአንድ የተሟላ ዓረፍተ ነገር ግለጽ/ጭ

8. በ1997 እ.ኤ.አ የሰላም ኖቤል ሽልማት ያገኙት በምን ምክንያት ነበር?

9. የምንባቡ ጥቅል መልእክት ምንድን ነው?

10. ከእማሆይ ትሬዛ ምን መማር እንችላለን?

**ምንባብ ሁለት፡- ቆሻሻና አወጋገዱ**

ቆሻሻ ከመኖሪያ ቤታችን፣ከቢሮወዎችና ከኢንዱስትሪዎች እያወጣን የምንጥለዉ የማይፈለግ ነገር ነዉ፡፡ ቆሻሻ ሲባል በየቦታዉ **ተዝረክርኮ** ወይም በየቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ዉስጥ ያለ ደረቅ ቆሻሻ፣አለዚያም እርጥብ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁላችንም ቁርጥራጭ ወረቀቶችን፣የምግብ ትራፊቆችን ወይም ሌሎች ነገሮችን በምንጥልበት ወቅት ቆሻሻ እንፈጥራለን፡፡ የኢንዱስትሪ ምርቶች በሚመረቱበት ጊዜም ቆሻሻ ይፈጠራል፡፡

ቆሻሻ ቁጥጥር ካልተደረገበትና በማንኛዉም ቦታ የሚጣል ከሆነ፣በአካባቢና በሰዉ ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ስለዚህም ፣አፈርን ወይም ዉሃን በማይበክልበት ቦታና ሰዎችም በዚሁ ሳቢያ ለአደጋ **በማይጋለጡበት** ሁኔታ ማስወገድ አለብን፡፡

ማንኛዉም የቆሻሻ ዓይነት በአግባቡ ካልተያዘ እኛንና አካባቢን ሊጎዳ ይችላል በአግባቡ **የአካባቢንእይታ** ያበላሻል፤መጥፎ ጠረን ያስከትላል። ለዝንቦች፣ለአይጦችና ልዩ ልዩ ተዋህስያን መራቢያ በመሆን በሽታ እንዲሰራጭ ያደርጋል። ዕፅዋትን፣ እንስሳትንና ሰዎችን ይመርዛል። አየርና ዉሃን **ይበክላል**። የረጅም ጊዜ ጎጂ ተፅኖዉ ደግሞ መርዛማ ኬሚካሎች በአካባቢዉ ዉስጥ ሳይሰባበሩ መቆየታቸዉና በአየርና በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ጉዳት ማድረሳቸዉ ነዉ።

ሁላችንም ብንሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቆሻሻ ስለምንፈጥርና ይህም ቆሻሻ ብክለትን ስለሚያስከትል፣በአግባቡ የመያዝ ኃላፊነት አለብን። የቆሻሻ አያያዝ በአራት ደረጃዎች ይካሄዳል። ይህም **የተቀናጀ** የቆሻሻ አያያዝ ይባላል። የመጀመሪያዉ ደረጃ ኢንዱስትሪዎች በተቻለ መጠን አነስተኛ ቆሻሻ የሚፈጠርበትን የአመራረት ሂደት መከተላቸዉ ነዉ። ይህ በንፁህ የአመራረት ሂደት መጠቀም ይባላል። ሁለተኛዉ እርምጃ ተመልሶ ጥቅም ላይ ሊዉል የሚችለዉን ማንኛዉንም ነገር ከቆሻሻ መለየት ነዉ። ይህ ቆሻሻን መልሶ መጠቀም ወይም ሀብት **እንዲያገግም** ማድረግ ይባላል። ሶስተኛዉ እርምጃ እያንዳንዱን የቆሻሻ ዓይነት አነስተኛ ቦታ እንዲይዝ አድርጎ **ማጨቅና** ጉዳቱ እንዲቀንስ ማጣራት ነዉ። አራተኛዉ እርምጃ ከላይ የተጠቀሱት ተግባሮች ከተከናወኑ በኋላ የሚቀረዉን ማንኛ ዉንም ቆሻሻ በአግባቡ ተጠንቶ ወደ ተሠራ የቆሻሻ መጣያ ወስዶ መጣል ነዉ።

ከላይ በተጠቀሱት መንገዶች ቆሻሻን ከምንጩ ጀምሮ እስከሚወገድበት ስፍራ ድረስ የሚደረግ ክንዉን፣ቆሻሻን ከምንጩ እስከ መቀበሪያዉ የመቆጣጠር መርሆ ይባላል። ይህንን መርሆ በመተግበር **የምናልመዉን** ንጹህ አካባቢ መፍጠር **ፋይዳዉ** ብ ዙ ነዉና ዛሬዉኑ ለተግባር እንነሳ።

(ከ9ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሃፍ (2004ዓ.ም) ከገጽ121-122፣ በመጠኑ መሻሻል ተደርጎበት የቀረበ)

***መመሪያ ሶስት***፡ ከተራ ቁጥር 11-20 ያሉትጥያቄዎች በምንባብ ሁለት መሰረት የቀረቡ ናቸው። ምንባቡን በጥንቃቄ በማንበብ ቀጥሎ ከ11-15 የቀረቡትን ጥያቄዎች የያዙት ሃሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት በተዘጋጀው መልስ መስጫ ወረቀት መልስ/ሽ

11.የቆሻሻ አያያዝ በአምስት ደረጃዎች ይካሄዳል።

12.መርዛማ ኬሚካሎች ሳይሰባበሩ መቆየታቸዉ ጉዳቱ ወዲያዉ የሚታይና ወዲያዉ ሊወገድ የሚችል ነዉ፡፡

13.ቆሻሻን በአግባቡ የመያዝ ሐላፊነት የከተማ ማዘጋጃ ቤቶች ነዉ፡፡

14.የቆሻሻ አያያዝ አራት ደረጃዎች አሉት፡፡

15.በንፁህ የአመራረት ሂደት መጠቀም ከኢንዱስትሪዎች ማምረት ጋር የተያየዘ ነዉ፡፡

***መመሪያ አራት***፡ ከተራ ቁጥር 11-20 ያሉትጥያቄዎች በምንባብ ሁለት መሰረት የቀረቡናቸው፡፡ ምንባቡን በጥንቃቄ በማንበብ 16-20 ላሉት ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች ትክክለኛ መልስ የያዘ ሆሄ በመምረጥ ለእያንዳንዱ ጥያቄ በተዘጋጀው መልስ መስጫ ወረቀት ላይ ሙላ/ይ፡፡

16.ቆሻሻን በሚመለከት ትክክል ያልሆነዉ የትኛዉ ነዉ?

ሀ) ኢንዱስትሪዎች በሚያመርቱበት ጊዜ ቆሻሻ ይፈጠራል፡፡

ለ) ቁርጥራጭ ወረቀቶች ንፁህ ይሁኑእንጂ፣የትም ቢጣሉ ቆሻሻ አይባሉም፡፡

ሐ) ማንኛዉም ቆሻሻ ሰዉን ሊጎዳ ይችላል፡፡

መ) ማጨቅና ማጣራት ሶስተኛዉ የቆሻሻ አያያዝ ደረጃ ነዉ፡፡

17.በአራት ደረጃዎች የሚካሄድ የቆሻሻ አያያዝ ---------------- የቆሻሻ አያያዝ ይባላል፡፡

ሀ) የተቀናጀ　　　　ሐ) ንፁህ

ለ) ፍትህ　　　　መ) የኢንዱስትሪ

18.በአግባቡ ያልተያዘ ቆሻሻ በሽታን እንዲሰራጭ የሚያደርገዉ በምንድን ነዉ?

ሀ) መጥፎ ጠረን በማምጣት፣　　　　ሐ) የልዩ ልዩ ተዋህስያን መራቢያ በመሆን፣

ለ) የአካባቢ እይታን በማበላሸት፣　　　　መ) ጠጣር ሆኖ ለብዙ ጊዜ በመቆየት

19.ጥቅም ላይ ሊዉል የሚችለዉን ነገር፣ ከቆሻሻ መለየት ----------- ይባላል፡፡

ሀ) ሀብትን እንዲያገግም ማድረግ፣　　　　ሐ) ማጣራት

ለ) ምርትን መልሶ መጠቀም፣　　　　መ) ከብከላ ማፅዳት

20.ቆሻሻን በጥናት ወደ ተሰራ መጣያ ወስደን ከመጣላችን በፊት መከናወን ያለበት ተግባር የትኛዉ ነዉ?

ሀ) በንፁህ የአመራረት ሂደት መጠቀም　　　　ሐ) ማጨቅና ማጣራት

ለ) ሀብት እንዲያገግም ማድረግ　　　　መ) ቆሻሻን ከምንጩ ማድሬቅ

## አባሪ ሐ፤ የጽሁፍ መጠይቁና የአንብቦ መረዳት ፈተናው አስተማማኝነት ፍተሻ

### አባሪ ሐ1፤ የጽሁፍ መጠይቁን አስተማማኝነት በክሮምባህ አልፋ ለመለካት ሲባል በሙከራ ጥናቱ ወቅት የተሰበሰበ መረጃ

| ተሳታፊ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | ድምር (ከ80 ነጥብ) |
| 1 | 2 | 5 | 2 | 4 | 2 | 4 | 5 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 5 | 4 | 1 | 4 | **50** |
| 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 2 | 1 | 3 | 4 | 2 | 5 | 3 | 5 | **49** |
| 3 | 2 | 5 | 2 | 2 | 1 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 2 | 4 | 5 | 2 | 3 | 3 | **52** |
| 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 4 | 4 | 5 | 4 | 4 | 4 | **59** |
| 5 | 1 | 4 | 1 | 2 | 4 | 5 | 2 | 1 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **31** |
| 6 | 2 | 5 | 4 | 1 | 1 | 2 | 5 | 2 | 4 | 2 | 1 | 5 | 2 | 2 | 2 | 2 | **42** |
| 7 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 5 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | **51** |
| 8 | 2 | 1 | 2 | 4 | 5 | 4 | 2 | 4 | 5 | 5 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | **59** |
| 9 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 3 | 5 | 1 | 5 | 3 | 1 | **65** |
| 10 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 4 | 4 | 5 | 4 | 1 | 5 | 4 | 3 | 4 | 4 | 5 | **58** |
| 11 | 2 | 4 | 5 | 3 | 4 | 5 | 4 | 4 | 3 | 4 | 5 | 1 | 5 | 4 | 5 | 3 | **61** |
| 12 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 1 | 4 | 4 | 3 | 5 | 3 | 3 | 2 | 3 | **52** |
| 13 | 4 | 1 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 5 | 4 | 4 | **60** |
| 14 | 3 | 2 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 3 | 5 | 3 | 4 | 3 | 3 | **60** |
| 15 | 2 | 1 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 2 | 3 | 5 | 4 | **63** |
| 16 | 1 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 1 | 2 | 3 | 1 | **35** |
| 17 | 4 | 1 | 4 | 1 | 4 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 4 | 4 | 5 | 2 | 3 | **56** |
| 18 | 1 | 4 | 1 | 3 | 1 | 5 | 1 | 3 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 3 | 2 | **32** |
| 19 | 4 | 1 | 5 | 1 | 4 | 1 | 5 | 1 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 1 | 5 | 1 | **48** |
| 20 | 4 | 2 | 1 | 3 | 5 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 5 | 1 | 1 | 5 | 2 | 3 | **52** |
| 21 | 1 | 4 | 5 | 1 | 5 | 1 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | **60** |
| 22 | 1 | 1 | 1 | 3 | 1 | 3 | 1 | 4 | 1 | 2 | 1 | 3 | 3 | 1 | 2 | 1 | **29** |
| 23 | 3 | 2 | 4 | 3 | 5 | 4 | 5 | 1 | 5 | 1 | 4 | 5 | 5 | 5 | 3 | 4 | **59** |
| 24 | 5 | 4 | 5 | 4 | 5 | 5 | 5 | 5 | 5 | 4 | 5 | 1 | 4 | 5 | 4 | 5 | **71** |
| 25 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 5 | 1 | 4 | 1 | 5 | 4 | 3 | 5 | 4 | 5 | 5 | **59** |
| 26 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 5 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | **60** |
| 27 | 5 | 2 | 5 | 1 | 4 | 3 | 5 | 2 | 5 | 3 | 5 | 4 | 3 | 5 | 3 | 5 | **60** |
| 28 | 2 | 5 | 2 | 4 | 2 | 4 | 5 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 5 | 4 | 1 | 4 | **50** |
| 29 | 4 | 3 | 2 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 2 | 1 | 3 | 4 | 2 | 5 | 3 | 5 | **49** |
| 30 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 3 | **26** |

## አባሪ ሐ2፤ አንብቦ መረዳት ፈተናውን አስተማማኝነት በKuder-Richardson (KR-20) ለመለካት ሲባል በሙከራ ጥናቱ ወቅት የተሰበሰበ መረጃ

| ID | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | ድምር ከ20 |
| 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | **12** |
| 2 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **11** |
| 3 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | **8** |
| 4 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | **12** |
| 5 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **19** |
| 6 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | **6** |
| 7 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | **6** |
| 8 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **10** |
| 9 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **15** |
| 10 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **14** |
| 11 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | **10** |
| 12 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **19** |
| 13 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | **10** |
| 14 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | **16** |
| 15 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | **14** |
| 16 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **10** |
| 17 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **18** |
| 18 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | **15** |
| 19 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | **12** |
| 20 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | **14** |
| 21 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **13** |
| 22 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | **19** |
| 23 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | **13** |
| 24 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **14** |
| 25 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | **8** |
| 26 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | **6** |
| 27 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | **9** |
| 28 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | **15** |
| 29 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 1 | **12** |
| 30 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | **8** |


**አባሪ መ፤ በጽሁፍ መጠይቅ እና በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰቡት የዋናው ጥናት መረጃዎች እሙኖች ፍተሻ መረጃዎች**

**አባሪ መ1፤ በጽሁፍ መጠይቅ እና በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰቡት የዋናው ጥናት መረጃዎች የስርጭት ወጥነት ፍተሻ**

| ተላውጦ | የግድለት ዜድ ውጤት | የዝብጠት ዜድ ውጤት |
|---|---|---|
| ማህበረ ስሜታዊ ብልሃት | -1.49 | -1.59 |
| ራስን ማበረታታት | -1.50 | -1.60 |
| ጭንቀትን መቀነስ | -1.88 | 1.61 |
| በትብብር መስራት | -1.49 | -1.77 |
| መጠየቅ | -1.81 | 0.67 |
| አንብቦ መረዳት | -0.98 | -1.18 |

አባሪ ሐ2፤ ተንባይ ተላውጦዎች ከተተንባይ ተላውጦ ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ ያላቸው ስለመሆኑ


የተካሄደ የብትን ግራፍ ፍተሻ፤




### አባሪ መ3፤ የፈርጀብዙ ተዛምዶ (multicollinearity) አለመኖር ፍተሻን ውጤት

| ተ.ቁ | ነጻ ተላውጦ | የTolerance | የVIF ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | ራስን የማበረታታት ብልሃት | .376 | 2.660 |
| 2 | ጭንቀትን የመቀነስ ብልሃት | .413 | 2.423 |
| 3 | በትብብር የመስራት ብልሃት | .529 | 1.891 |
| 4 | የመጠየቅ ብልሃት | .343 | 2.911 |

### አባሪ መ4፤ Homoscedasticity (በነጻ ተላውጦዎቹ ባለው እያንዳንዱ ዋጋ ትይዩ በጥገኛው ተላውጦ የሚገኙ ዋጋዎች መደበኛ ልይይት ተመሳሳይነት) ፍተሻ ውጤቶች





Partial Regression Plot
Dependent Variable: Reading Comprehension
Reading Comprehension
5.0
2.5
.0
-2.5
-5.0
-6
-3
0
3
6
Encouraging yourself


Partial Regression Plot
Dependent Variable: Reading Comprehension
Reading Comprehension
5.0
2.5
.0
-2.5
-5.0
-5.0
-2.5
.0
2.5
5.0
Lowering anxiety


Partial Regression Plot

Dependent Variable: Reading Comprehension




Partial Regression Plot

Dependent Variable: Reading Comprehension



## አባሪ ሠ፤ በጽሁፍ መጠይቅ እና በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰቡ የዋናው ጥናት መረጃዎች

### አባሪ ሠ1፤ በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ የዋናው ጥናት መረጃዎች

| ተሳታፊ | አራቱ የማህበረ ስሜታዊ መጠይቅ ክፍሎች | | | | (የማህበረ ስሜታዊ ብልሃት ክፍሎች በአንድነት (80 ነጥብ) |
|---|---|---|---|---|---|
| | ራስን ማበረታታት (20 ነጥብ) | ጭንቀትን መቀነስ (20 ነጥብ) | በትብብር መስራት (20 ነጥብ) | መጠየቅ (20 ነጥብ) | |
| 1 | 12 | 14 | 12 | 13 | 51 |
| 2 | 8 | 14 | 16 | 15 | 53 |
| 3 | 11 | 13 | 11 | 19 | 54 |
| 4 | 10 | 9 | 12 | 16 | 47 |
| 5 | 8 | 15 | 13 | 8 | 44 |
| 6 | 9 | 13 | 15 | 8 | 45 |
| 7 | 13 | 12 | 17 | 10 | 52 |
| 8 | 13 | 16 | 17 | 18 | 64 |
| 9 | 13 | 16 | 14 | 16 | 59 |
| 10 | 13 | 16 | 12 | 16 | 57 |
| 11 | 15 | 17 | 14 | 16 | 62 |
| 12 | 12 | 11 | 15 | 11 | 49 |
| 13 | 14 | 14 | 13 | 16 | 57 |
| 14 | 14 | 16 | 20 | 16 | 66 |
| 15 | 12 | 15 | 18 | 19 | 64 |
| 16 | 15 | 17 | 16 | 16 | 64 |
| 17 | 12 | 17 | 12 | 13 | 54 |
| 18 | 12 | 11 | 14 | 12 | 49 |
| 19 | 9 | 14 | 14 | 8 | 45 |
| 20 | 14 | 19 | 16 | 15 | 64 |
| 21 | 10 | 19 | 20 | 13 | 62 |
| 22 | 13 | 7 | 12 | 11 | 43 |
| 23 | 13 | 19 | 19 | 17 | 68 |
| 24 | 17 | 20 | 19 | 19 | 75 |
| 25 | 11 | 18 | 17 | 14 | 60 |
| 26 | 15 | 17 | 15 | 14 | 61 |
| 27 | 15 | 19 | 11 | 18 | 63 |
| 28 | 15 | 20 | 16 | 20 | 71 |
| 29 | 17 | 16 | 20 | 19 | 72 |
| 30 | 15 | 9 | 12 | 9 | 45 |
| 31 | 20 | 20 | 20 | 16 | 76 |
| 32 | 9 | 10 | 13 | 10 | 42 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 33 | 20 | 18 | 19 | 20 | 77 |
| 34 | 16 | 18 | 14 | 16 | 64 |
| 35 | 20 | 20 | 16 | 20 | 76 |
| 36 | 20 | 20 | 16 | 20 | 76 |
| 37 | 16 | 16 | 17 | 18 | 67 |
| 38 | 16 | 16 | 18 | 16 | 66 |
| 39 | 20 | 18 | 19 | 20 | 77 |
| 40 | 20 | 19 | 17 | 16 | 72 |
| 41 | 20 | 20 | 19 | 20 | 79 |
| 42 | 12 | 13 | 16 | 14 | 55 |
| 43 | 12 | 15 | 14 | 16 | 57 |
| 44 | 16 | 16 | 14 | 16 | 62 |
| 45 | 16 | 15 | 15 | 14 | 60 |
| 46 | 20 | 19 | 20 | 20 | 79 |
| 47 | 16 | 17 | 17 | 16 | 66 |
| 48 | 19 | 18 | 18 | 18 | 73 |
| 49 | 17 | 18 | 16 | 16 | 67 |
| 50 | 16 | 16 | 17 | 16 | 65 |
| 51 | 16 | 16 | 17 | 16 | 65 |
| 52 | 19 | 20 | 19 | 20 | 78 |
| 53 | 20 | 20 | 20 | 20 | 80 |
| 54 | 16 | 9 | 13 | 13 | 51 |
| 55 | 15 | 16 | 13 | 13 | 57 |
| 56 | 10 | 12 | 14 | 12 | 48 |
| 57 | 11 | 13 | 15 | 14 | 53 |
| 58 | 20 | 19 | 14 | 17 | 70 |
| 59 | 16 | 17 | 15 | 17 | 65 |
| 60 | 20 | 17 | 20 | 20 | 77 |
| 61 | 12 | 16 | 11 | 13 | 52 |
| 62 | 16 | 16 | 16 | 16 | 64 |
| 63 | 16 | 16 | 16 | 16 | 64 |
| 64 | 20 | 20 | 18 | 20 | 78 |
| 65 | 13 | 13 | 16 | 13 | 55 |
| 66 | 15 | 16 | 16 | 16 | 63 |
| 67 | 20 | 19 | 19 | 19 | 77 |
| 68 | 13 | 15 | 17 | 16 | 61 |
| 69 | 19 | 20 | 17 | 16 | 72 |
| 70 | 20 | 19 | 19 | 20 | 78 |
| 71 | 15 | 16 | 17 | 16 | 64 |
| 72 | 17 | 14 | 18 | 16 | 65 |
| 73 | 16 | 16 | 17 | 16 | 65 |
| 74 | 20 | 20 | 19 | 20 | 79 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 75 | 18 | 20 | 19 | 20 | 77 |
| 76 | 18 | 17 | 15 | 16 | 66 |
| 77 | 18 | 16 | 15 | 16 | 65 |
| 78 | 19 | 20 | 20 | 20 | 79 |
| 79 | 20 | 19 | 18 | 19 | 76 |
| 80 | 19 | 18 | 19 | 20 | 76 |
| 81 | 17 | 18 | 17 | 18 | 70 |
| 82 | 17 | 17 | 18 | 17 | 69 |
| 83 | 16 | 17 | 19 | 18 | 70 |
| 84 | 20 | 20 | 19 | 18 | 77 |
| 85 | 19 | 19 | 19 | 19 | 76 |
| 86 | 20 | 19 | 18 | 19 | 76 |
| 87 | 16 | 16 | 18 | 17 | 67 |
| 88 | 19 | 20 | 19 | 20 | 78 |
| 89 | 20 | 18 | 19 | 17 | 74 |
| 90 | 20 | 20 | 20 | 20 | 80 |
| 91 | 20 | 20 | 19 | 20 | 79 |
| 92 | 20 | 19 | 20 | 20 | 79 |
| 93 | 15 | 16 | 15 | 15 | 61 |
| 94 | 16 | 18 | 16 | 16 | 66 |
| 95 | 13 | 13 | 13 | 15 | 54 |
| 96 | 15 | 16 | 17 | 16 | 64 |
| 97 | 16 | 14 | 15 | 15 | 60 |
| 98 | 16 | 16 | 17 | 16 | 65 |
| 99 | 20 | 18 | 19 | 20 | 77 |

**አባሪ ሠ2፤ በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰቡ የዋናው ጥናት መረጃዎች**

| ተሳታፊ | ውጤት (ከ20 ነጥብ) |
|---|---|
| 1 | 12 |
| 2 | 20 |
| 3 | 19 |
| 4 | 16 |
| 5 | 10 |
| 6 | 13 |
| 7 | 16 |
| 8 | 18 |
| 9 | 17 |
| 10 | 15 |

| | |
|---|---|
| 11 | 16 |
| 12 | 13 |
| 13 | 14 |
| 14 | 20 |
| 15 | 20 |
| 16 | 14 |
| 17 | 14 |
| 18 | 11 |
| 19 | 10 |
| 20 | 14 |
| 21 | 20 |
| 22 | 11 |
| 23 | 18 |
| 24 | 19 |
| 25 | 15 |
| 26 | 15 |
| 27 | 18 |
| 28 | 18 |
| 29 | 19 |
| 30 | 10 |
| 31 | 13 |
| 32 | 9 |
| 33 | 20 |
| 34 | 14 |
| 35 | 17 |
| 36 | 17 |
| 37 | 15 |
| 38 | 16 |
| 39 | 17 |
| 40 | 17 |
| 41 | 15 |
| 42 | 13 |
| 43 | 12 |
| 44 | 13 |
| 45 | 10 |
| 46 | 20 |
| 47 | 16 |
| 48 | 18 |
| 49 | 15 |
| 50 | 16 |

| | |
|---|---|
| 51 | 16 |
| 52 | 17 |
| 53 | 17 |
| 54 | 16 |
| 55 | 10 |
| 56 | 10 |
| 57 | 12 |
| 58 | 13 |
| 59 | 16 |
| 60 | 17 |
| 61 | 12 |
| 62 | 12 |
| 63 | 14 |
| 64 | 13 |
| 65 | 12 |
| 66 | 15 |
| 67 | 18 |
| 68 | 12 |
| 69 | 17 |
| 70 | 17 |
| 71 | 13 |
| 72 | 13 |
| 73 | 14 |
| 74 | 20 |
| 75 | 18 |
| 76 | 14 |
| 77 | 14 |
| 78 | 18 |
| 79 | 19 |
| 80 | 19 |
| 81 | 16 |
| 82 | 15 |
| 83 | 17 |
| 84 | 16 |
| 85 | 15 |
| 86 | 16 |
| 87 | 15 |
| 88 | 17 |
| 89 | 18 |
| 90 | 18 |

| | |
|---|---|
| 91 | 19 |
| 92 | 19 |
| 93 | 14 |
| 94 | 14 |
| 95 | 16 |
| 96 | 15 |
| 97 | 17 |
| 98 | 13 |
| 99 | 17 |
| 100 | 13 |